# ጥላ TILA

ጥላ ግንቦት 2004 ዓ.ም አንደኛ ዓመት ቁ 2 TILA May 2012 First Year 2nd Edition

# በፖለቲካችን ሁሉም አትሌት መሆን ነው ያለበት!!



## አዲዮስ ሮሜሲ!

## No More Joseph Konys!!





# ጥላ መፅሄት የአድራሻ ለውጥ አደረገች

**ጥላ መፅሄት አዲስ የአድራሻ ለውጥ ስላደረገች በሚከተሉት ስልክ ቁጥሮች በመደወል አዲሱን አድራሻ ማግኘት ትችላላችሁ።**

**0152-22195567**
**0176-593844**
**0176-68830082**
**0176-71668780**

**መስፍን አብርሃ፤እየሩሳሌም ሱሞሮ ወይም ዳዊት ፋንታ ብላችሁ ማነጋገር ትችላላችሁ።**

**መልካም ጊዜንም እንመኝላችሁዋለን!**


## ማስታወቂያ

በጀርመን አገር በሚታተሙት መፅሄቶች የህትመት ጊዜ ርዝመት ምክንያት ሃሳቦትን/ፅሁፎትን በአፋጣኝ ለንባብ ለማብቃት ተቸግረዋል?የስብሰባና የሰላማዊ ሰልፍ ፎቶዎቾስ በኢንተርኔት እንዲለቀቅሎት ይፈልጋሉ? እንግዲያውስ በአገሪቱ ጠበቆች አድናቆትና እውቅና የተቸረው ጥላ መፅሄት ፈጣንና ፍላጎቶን አርኪ አገልግሎት ለመስጠት ተዘጋጅቷል።

እኛን ለማግኘት ሶስተኛ ወገን አያስፈልጎትም!በቀጥታ ይደውሉልን መረጃዎትን ተቀብለን ፍላጎቶን እናሟላለን።

በአሜሪካና በአውሮፓ ከሚገኙ አገር በቀል መገናኛ ብዙሃን ጋር ባለን ግንኙነት መሰረት በጥላ መፅሄትና ዌብ ሳይት መረጃዎትን አስተላለፉ ማለት ምን አለፋዎት አላማዎት ተሳካ ማለት ነው።
እንግዲያውስ በፈለጉት ቀንና ሰዓት በተለመዱት አድራሻዎቻችን ያገኙናል፡፡

Mesfin Abraha
Wehneberger Straße 63
36251 Bad Hesfeld
Tel. 0152 2219 5567
0176 5938 4456
E-Mail. tilamagazine@yahoo.de
Web-Site. Tilamagazine.yolasite.com

ጥላ መፅሄት የእናንተው ናት!

# ጥላ


ዋና ስራ አስኪያጅ General Manager
መስፍን አብርሃ Mesfin Abraha

ዋና አዘጋጆች Editor In Chiefs
እየሩሳሌም ሱሞሮ Eyerusalem Sumoro
ብሩክ ገ/መስቀል Biruk G/Meskel
ዳዊት ፋንታ Dawit Fanta

አዘጋጆች Editors
ዮሃንስ ሳምሶን Yohannes Samson
ብሩክ ሃይሉ Biruk Hailu

ፅሁፍ አስተባባሪዎች Coordinators
ዮሴፍ ክፍሌ Yosef Kifle
ኤደን ዳዊት Eden Dawit
ዳንኤል ፋንታ Daneil Fanta

የኮምፒዩተር ፅሁፍ ቅንብር Computer Graphics
ሩት ተሰማ Rut Tessema
ህሊና ዳዊት Hilina Dawit

ሌይአውትና ዲዛይን Layout & design
እየሩሳሌም ሱሞሮ Eyerusalem Sumoro

የካርቱን ስዕል Cartoonist
ብሩክ ገ/መስቀል Biruk G/Meskel



የጥላ መፅሄት አድራሻ /Tila Magazine Address
Mesfin Abraha
Wehneberger Str.63
36251 Bad Hersfeld
E-Mail:- tilamagazine@yahoo.de
Web- Site:- tilamagazine.yolasite.com
Tel.No.:- 0152 22195567, 0176 59384456 ,0176 68830082


# ማውጫ


| | ገጽ |
|---|---|
| በኢትዮጵያ ፖለቲካ ሁላችንም አትሌቶች መሆን ነው ያለብን። | |
| አንዱ ሯጭ ሌላው ተመልካች የሚባል ነገር አይሰራም!!! | 7 |
| የነበልባሉ ዘመን ይብቃን | 12 |
| ወዴት እየሄድን ነው? | 12 |
| ታሪክን ለማጥፋት የተነሣ ስርዓት | 12 |
| ቅጥ ያጣው የወያኔ ትንኮሳ | 12 |
| ኧረ ወገን! ምን እስክንደረግ ነው የምንጠብቀው? | 13 |
| ዴሞክራሲ ለማን? | 13 |
| በዘር የተከፋፈለ የወያኔ ዲሞክራሲ | 14 |
| ጊዜው አሁን ነው | 14 |
| የተዘባረቀ ህልም | 14 |
| “በዲሞክራሲ ከለላ“ | 14 |
| ወያኔ እጅህን ከሃይማኖቶች ላይ አንሳ! | 15 |
| ሴቶችን ያላማከለው የወያኔ ፖሊሲ | 15 |
| ዴሞክራሲ የተፈጥሮ ፀጋ እንጂ የአምባገነኖች ችሮታ አይደለም!! | 15 |
| በታሪክ አሻራዎቻችን ላይ የሚደረገው ዘመቻ ይቁም! | 16 |
| የፖለቲካዊ ስርዓት ተስፋ አስቀራጭነት | 16 |
| አምባገነኑ የወያኔ መንግስት እስከመቼ? | 16 |
| የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ውጤት በኢትዮጵያ | 17 |
| በህዝብህ ላይ ጭካኔ | 17 |
| ዲሞክራሲ በጭልፋ | 17 |
| የዋጋ ንረት በኢትዮጵያ | 17 |
| የሴቶች መብት በኢትዮጵያ | 18 |
| የወያኔን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት እቅድ እንቋቋም! | 18 |
| እውነት የምንሰማው መቼ ነው | 18 |
| ወያኔና የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መሪ እጅና ጓንት መሆናቸውን ያውቃሉ? | 19 |
| የመኖሪያ ቤት መስሪያ መሬት ምሪት በኢትዮጵያ | 19 |
| ነጻነት ወይስ ባርነት | 20 |
| መታገል ወንጀል ሆነ | 20 |
| የሥነ ምግባር መርሆች እና ባለስልጣናት | 21 |
| ነጻነት የፖለቲካ እስረኞች | 21 |

# ማውጫ

ገጽ


| | |
|---|---|
| ካርቶን ስእል | 22 |
| Due Process in Ethiopia | 23 |
| Our political leadership Problem | 23 |
| Woyane- Unfair regime! | 24 |
| **Shame on Meles** | **25** |
| Was hat er zu verstecken? | 25 |
| Many Oromos arrested by TPLF forces and Disappeared!!! | 26 |
| Everything is possible | 27 |
| EPRDF (TPLF) Recent propaganda | 27 |
| Start Journey to Freedom! | 27 |
| We need to be like Tunisians! | 28 |
| The Deadlock of Ethiopia's Human Rights Protection | 29 |
| Ethiopian women shall stand up for freedom! | 30 |
| Abuse of human rights in Ethiopia | 31 |
| No Excuse to woyane! | 31 |
| One day | 32 |
| Human Rights Paradox in Ethiopian Government acts Vis- A -Vis constitutional framework | 32 |
| አይዘጋም አፌ | 33 |
| አይለይም ወይ ዛሬስ የወያኔ ኑሮ | 33 |
| ወያኔ የታሪክ አተላው | 33 |
| እነ አሉ- ምን አሉ? | 33 |
| የፍፃሜው ጦርነት | 34 |
| አብሮ አደግ መከራዬ | 34 |
| ዶሮይቱ ህይወት | 34 |
| ይለይ ነፃነቱ ወይ ባርነታችን! | 35 |
| ምን እናውርሳቸው | 35 |
| አዲዎስ ሮሜሲ! | 36 |



# Editorial

## We Need a Political Resurrection!!!

The resurrection is the return of the body to life. Life is the principle of man's existence, for when God created man He breathed into his nostrils the breath of life, so man became a living being (Gen 2: 7).

We celebrated two weeks ago this year`s 2012 Jesus Christ Resurrection. But, we Ethiopians need this time a real political resurrection. “Losing really hurts, but you learn a lot from it,” An American Republican Party Senate member Andrews said in a brief interview. “You learn what your weaknesses are and you look how to compensate for them, and I hope that I’ve become a better public servant by learning from defeat or loose.” Underscores Andrew

As Ethiopian we lost a lot of chances and opportunities to have a good government. Reading along the Ethiopian history, we found our self thinking about the politics of resurrection. We barely know what nonviolent politics might look like. Most of us, from Mengistu to Meles to our relatives, local priest and bishop, uphold the politics of crucifixion. We support our military, justify our war-making, advocate revenge, pay for our drones, and even support executions. We honor those involved in the mass murder of war. Indeed, we kill people who kill people to show that killing people is wrong. We are experts at the politics of crucifixion.

We are told that our wars are necessary, our weapons defensive, our political program is the only alternative, and our democracy a sign of freedom. No alternative voices are permitted to speak. We urge people to boycott global Medias which propagate for the culture of revenge, Generalization, Untrustworthiness, dictatorship, communism, war and death.

But what about the politics of resurrection? As resurrection people, we have nothing to do with propaganda, war, segregation, clanism or what so ever. We do not support the forces of death. We do not bring death to anyone. We resist militarism and try to transform our culture of misguided and a divide and rule politics. We should have to be people of nonviolence, forgiveness, compassion and peace lovers. We see the right resurrection of Ethiopian Politics where there is no more death, no more war, no more segregation, no more famine, no more violence, no more tears.

The political implications of resurrection offer our only hope. If we believe in Ethiopian Politics resurrection, and look toward new politics of togetherness and Tolerance, then we are summoned into a new vocation of Nation building. We have to reject revenge, retaliation, killing and war, and join the nationwide campaign to abolish war, poverty, executions, exodus, segregation, clanism, divide and rule system and similar sub-continental destruction. **Tila magazine** brings you as usual new faces & ideas, opportunities and a special guest of honor. Have a nice reading!!!

**``Tila Magazine is yours Magazine!!!Tila is a magazine not only you read it, but also you will write on it! ``**



# ርዕሰ አንቀጽ

# የፖለቲካ ትንሳኤም ያስፈልገናል!

ትንሳኤ ማለት ከሞት ወደ ህይወት መመለስ ነው።ህይወት ደግሞ የፍጡራን የመኖር መርህ ነው።እግዚአብሄር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤በአፍንጫውም የህይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ፤ሰውም ህያው ነፍስ ያለው ሆነ።(ዘፍጥረት 2፡7)

ከሁለት ሳምንታት በፊት በመላው ዓለም የምንገኝ የክርስትና ሓይማኖት ተከታዮች የ2004 ዓ.ም የጌታችን የመድሃኒታችን የእየሱስ ክርስቶስን ትንሳኤ በዓል አክብረናል።ነገር ግን እኛ ኢትዮጵያውያን በዚህ ሰዓት ትክክለኛ የፖለቲካ ትንሳኤም ያስፈልገናል።አንድ አሜሪካዊ ሴናተር በ2008ቱ የአሜሪካ ምርጫ እንዲህ ብሎ ነበር ” መሸነፍ ወይም ዕድል ማጣት በእውነት በጣም ያበግናል ነገር ግን ከክስተቱ ብዙ መማር ይቻላል።ድክመቶችህ ምን እንደሆኑ ትማራለህ እንዲሁም እንዴት አድርገህ መካስ እንዳለብህም ትመለከታለህ።ተስፋ አደርጋለሁ ከውድቀቴ ወይም ከሽንፈቴ ብዙ ስለተማርኩ አሁን የተሻለ የህዝብ አገልጋይ ሆኛለሁ።”

እንደ ኢትዮጵያውያን ጥሩ መንግስት መመስረት የምንችልባቸው በርካታ አጋጣሚዎች ወይም ዕድሎች ከእጃችን አምልጠውናል።የኢትዮጵያን ታሪክ መለስ አድርገን ገልበጥ አድርገን ከፈተሽነውም አሁን ላይ የፖለቲካ ትንሳኤ ማድረግ እንደሚያስፈልገን ያሳስበናል።ይህንንም ለማድረግ ፀረ-ትርምስ የሆነ የፖለቲካ ስልትን ማወቅ ይበቃናል።አብዛኞቻችን በቀላሉ ከመንግስቱ እስከ መለስ ቤተሰቦቻችንን ጨምሮ ምዕመኑም የሃይማኖት መሪውም የስቅለት ፖለቲካን ስንደግፍ ኖረናል።ጦራችንን ግፋ ብለናል የምናካሂደው ጦርነትም ህጋዊ መሆኑን ሰብከናል ብቀላን ቀስቅሰናል ለፈንጂዎቻችንና ለቅንቡላዎቻችን ከፍለናል ይባስ ብለን ስንፈርድ ኖረናል።በጦርነት በርካቶችን የፈጀውን ስንሸልምና ስናሞግስም እንዲሁ።እንደ ሃሞራቢ ህግም መግደል ስህተት መሆኑን ለማሳየት ገዳዮችን እየገደልን ነው።ምንአለፋችሁ የስቀለው ፖለቲካ ባለሙያዎች(ኤክስፐርቶች)ሆነናል።

ጦርነታችን አስፈላጊ የጦር መሳሪያዎቻችን ተከላካይ የፖለቲካ ፕሮግራማችን ብቸኛ አማራጭ ዴሞክራሲያችን የነፃነት ምልክት ነው በሚል ትዕቢት ተወጥረን በአደባባይ እየደሰኮርን ነው።አማራጭ ድምፆች እንዲደመጡ በጭራሽ ዕድል አልሰጠንም።ህዝቡ በአገራችንም ይሁን በዓለም ላይ ያሉትን የብቀላ ባህል እንዲዳብር የጅምላ ፍረጃ እንዲጠናከር አለመተማመን እንዲሰፍን አምባገነንነትን ኮምዩኒዝምን ጦርነትንና ሞትን የሚሰብኩትን መገናኛ ብዙሃን ሊዘጋቸው ይገባል።

የፖለቲካ ትንሳኤ ናፋቂዎችንስ? እንደ ፖለቲካ ትንሳኤ ናፋቂዎች ከፕሮፓጋንዳ ከጦርነት ከዘር መለያየትና መድሎ እንዲሁም ከጎሰኝነት ጋር ምንም የሚያገናኘን የለም።የሞት እንቢልታ ነጋሪዎችን አንደግፍም ሞትንም ለማንም አናጓጓዝም።ወታደራዊነትን እናወግዛለን ከከፋፍለህ ግዛ መርህና ከተሳሳተ የፖለቲካ ባህልም ህዝባችን እንዲላቀቅ አበክረን መስራት ይጠበቅብናል።እኛ ኢትዮጵያውያን ፀረ-ትርምስ ይቅር የምንባባል ምህረት ባህላችን የሆነና አፍቃሪ ሰላም ልንሆን ይገባናል።

ኢትዮጵያ የፖለቲካም ትንሳኤ እንደሚያስፈልጋት ስናምንና ግባችን አዲስ የመቻቻልና የአብሮነት ፖለቲካዊ ግንባታ ሲሆን ነው የፖለቲካ ትንሳኤያችን ተፅእኖ መፍጠርና ለውጥ ማምጣት የሚችለው እንዲሁም አገራችንን እንደ አዲስ የመገንባት ብቃቱን የምናገኘው።የብቀላ የጥቃት የግድያና የጦርነት አስተሳሰቦችን በማስወገድ ኢትዮጵያችንን ከጦርነት ከረሃብ ከፍርደ ገምድል ከስደት ከዘር መድሎ ከጎሰኝነት ከከፋፍለህ ግዛ ስርዓትና ከተመሳሳይ የአካባቢ እልቂት ልንታደጋት የምንችለው።

ጥላ መፅሄት እንደተለመደው አዳዲስ ፊቶችንና ሃሳቦችን፤ዕድሎችንና ልዩ የክብር እንግዶችን ይዛ ባላችሁበት ደርሳለች።ቤት ለእምቦሳ በሏት።መልካም ንባብ!!!

**“ጥላ መጽሄት የእናንተው መፅሄት ናት!!! ጥላ የሚያነቧት ብቻ ሳትሆን የሚፅፉባትም መጽሄት ናት!”**

# About Tila
# Dear Readers

Realizing the fact that the digital age has empowered and made ordinary people across the world irrepressible beyond their imagination, **WE** aims to serve as a credible platform that will spread uncensored interviews, news, commentaries and analyses that are unlikely to see daylight in Ethiopia.

Fortunately, here is where you find **TILA**, the un-disputably best source of information serving the Ethiopian Diaspora community in Europe & America with a proven record of excellence in journalism.

**TILA** is a political magazine, published and distributed by patriotic Ethiopians around Hessen region in Germany, which appears in Amharic, English and Germany Languages every 3 months. It is a magazine of quality, responsibility and standard. Entertainment and sport are among our coverage issues next to Ethiopian politics.

As a reader, you are to get useful political and current news in **TILA** than any other publication can offer you. More comprehensive analysis and interpretations than any other media can present to you. In fact, these are some of the qualities of **TILA** that has made it the largest circulating magazine in its category. TILA magazine has also partnered with ethiomedia.com, ethiogermany.de and afroaddis.wordpress.com among others, to deliver reliable and high quality content to our visitors.

Don’t take the chance of missing this spectacular political magazine. Subscribe to it today!

We promise, you won’t regret your decision. Reach us on tilamagazine@yahoo.de & tilamagazine.yolasite.com

**Tila Magazine is yours Magazine!**

# ከአዘጋጆች
# ውድ አንባብያን

ጥላ መፅሄት በየሶስት ወሩ የሚታተም የፖለቲካ መፅሄት ነው።መፅሄቱ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሰረት አድርጎ በጀርመን አገር የሚታተም ቢሆንም መረጃ መረቦችን በመጠቀም መላውን ዓለም የማዳረስ ዓላማን አንግቦ እየተንቀሳቀሰ ነው።

የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታና ጠቃሚ መረጃዎችን በማካተት ዝናን ያተረፈው የጥምረት መፅሄት አዘጋጆች ያቋቋሙት ጥላ መፅሄት የስሙ ስያሜ እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች በተበታተነ ሁኔታ የሚያካሂዱትን የትግል ሂደት በማስቀረት በአንድ **ጥላ** ስር እንዲሰባሰቡ ለማሳሰብና አቅጣጫ ለመጠቆም ነው።

የፖለቲካ ሃይሎች በተበታተነ ትግላቸው ጋት እንኳን መራመድ እንደማይችሉ በመገንዘብ የጋራ ትግል እንዲያካሂዱ ለማበረታታትም ጭምር ነው እ.ኤ.አ ከጥር 2012 ጀምሮ በዚህ ስም መፅሄቱ እንዲጠራ የወሰንነው።በመፅሄቱ አዝናኝና አስተማሪ ዝግጅቶች የሚካተቱበት ሲሆን ስፖርትም ትኩረት ያገኛል።

ጥላ መፅሄት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሃሳቡን ያለምንም ገደብ በነፃነት የሚያቀርብበት ክፍት መድረክ በመሆኑ በመፅሄቱ የሚወጡት ፅሁፎች በሙሉ የፀሃፊዎቹን እንጂ የጥላ መፅሄት ዝግጅት ክፍልን የማይመለከቱ መሆናቸውንም መግለፅ እንወዳለን።

**ጥላ መፅሄት የእናንተው መፅሄት ነው!**

# በኢትዮጵያ ፖለቲካ ሁላችንም አትሌቶች መሆን ነው ያለብን። አንዱ ሯጭ ሌላው ተመልካች የሚባል ነገር አይሰራም!!!

## ኢትዮጵያዊው የሰው ልጆች መብት ተሟጋች (አክቲቪስት) ታማኝ በየነ

*ታማኝ በየነ ይሄው አለ፤*
*ሀገሬን ወገኔን ሰንደቁን እንዳለ፡*
*ነጻነት እኩልነት አንድነት እያለ፡*
*ኢትዮጵያ ሀገሬን አትንኩ እንዳለ።ድምፃዊ ደረጀ ደገፋው ነበር ለታማኝ ክብር በተዘጋጀ ምሽት ላይ ያቀነቀነለት!*

አክቲቪስት*ተሟጋች*ታማኝ በየነ(Activist Tamagne Beyene) ከወይዘሮ ማሚቴ ቢተውና ከግራዝማች በየነ ወንዲፍራው አብራክ ነው በሰሜን ጎንደር ጭልጋ ውስጥ ወደዚህ ዓለም የመጣው።ከጎንደር ባህል ቡድን ጀምሮ በብሄራዊ ትያትር በህዝብ ለህዝብ ትርዒት በሮሃ ባንድ በደመራ ባንድ እረ በስንቱ ብቻ ምን አለፋችሁ መድረክ አለ ከማለት ታማኝ አለ ማለት ይቀላል። በአገር ቤት እያለም በተለይ በመድረክ አስተዋዋቂነቱ አንቱ የተባለ ከመሆኑም በላይ ከአገር ሲወጣ ሙያውንም ጠራርጎ ይዞት ወጣ መሰል የሚተካውም አላገኘንም።በርካታውም የጥበብ አፍቃሪ መድረክ አስተዋዋቂነት በታማኝ ጊዜ ቀረ ብሎ የታማኝ ያለህ እያለ ነው።

ላለፉት 17 ዓመታት ኑሮውን በአሜሪካን አገር ያደረገው ታማኝ በየነ ካለፉት 10 ዓመታት ወዲህ ከአርቲስትነቱ በተጨማሪ የአክቲቪስትነቱን ተግባር በማቀላጠፍ አገራችንን በተመለከቱ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ በመገኘት የበኩሉን አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከፍተኛ ተደማጭነትን ያገኘው ታማኝ በየነ በአገራዊ መድረኮች ላይ ሁሉ በመገኘት ሶስተኛው ፓርቲ እስከመባል ደርሷል። አገራዊ መድረኮቹ ያለ ታማኝ ተሳታፊነት አይጥሙም የተባለ ይመስል ታማኝ የአገራዊ ጉዳይ መድረክ ቅመም ሆኗል ማለት ይቻላል።



የታዋቂዋ ድምፃዊት ፋንትሽ በቀለ ባለቤትና የ3 ልጆች አባት የሆነው ታማኝ በየነ በአሁኑ ወቅት እዛው በአሜሪካ አሌክሳንድሪያ ውስጥ ይኖራል።

ባልደረባችን ጋዜጠኛ መስፍን ኣብርሃ የጥላ መፅሄት የዚህ ወር እትም ልዩ የክብር እንግዳ የሆነውን ታማኝን በተለያዩ ግላዊ አገራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከሚኖርበት ከአሜሪካ አነጋግሮታል። መልካም ቆይታ ይሁንላችሁ።

**ጥላ፡-** በተለያዩ መድረኮች የህግ የበላይነት ላይ ትኩረት ሰጥተህ ስትናገር ትደመጣለህ።መነሻህ ምንድን ነው?

***ታማኝ፡-*** *መነሻዬ ስማችን ነው።እንደ ጨው ዘር ተበትነን ኢትዮጵያዊ ስደተኛ በየትኛውም የዓለም ክፍል ኢትዮጵያዊ ስደተኛ በየትኛውም አገር እስር ቤቶች ውስጥ የሚሰቃይ ዜጋ ሆኗል።ይሄ ሁሉ ለምን ሆነ ብለን ስናይ ደግሞ መልሱ ቀላል ሆኖ እናገኘዋለን።በአገራችን የህግ የበላይነት ባለመኖሩ ዜጎች የሚተዳደሩት በአምባገነን ግለሰቦች መልካም ፈቃድ በመሆኑ ነው የህግ የበላይነት ይኑር በአገራችን ብዬ የምጮኸው።*

**ጥላ፡-** *ታማኝ ፖለቲከኛ ሆኗል ለይቶለታል የሚሉህ አሉ።ለመሆኑ የግንቦት ሰባት ወይም የሌላ የፖለቲካ ድርጅት አባል ነህ እንዴ?*

***ታማኝ፡-*** *ታማኝ ፖለቲከኛ ሆኗል ለይቶለታል የሚለው ቋንቋው በራሱ ትክክል አይደለም።በዚህ የሚገኝ ጥቅም የለም።ለሌሎች መብት መጮህ የራስህን የቤተሰብህን የልጆችህን ጊዜ መስዋዕት አድርገህና ምቾት ይቅርብኝ ብለህ ለሰው ልጆች መብት መታገል ለይቶለታል የሚያስብል አይደለም።መብቴን አውቄ ልሂድ ሌሎችም መብታቸውን ይወቁ ነው የእኔ መንገድ።እኔ እኮ ሌሎች ታግለው ነፃ ባወጧት አገር ነው የምኖረው። ስለዚህ ለአገሬ ደግሞ እኔና ሌሎችም ኢትዮጵያውያን ነን ልንታገልላት የሚገባው ማንንም እንዲመጣና ነፃ እንዲያወጣን መጠበቅ ተገቢም ትክክልም አይደለም።ስለዚህ እኔ የማንም የፖለቲካ ድርጅት አባል አይደለሁም።ትናንት ህወሓት ኢትዮጵያን ሲቆጣጠር ብቻዬን ቆሜ እንደተናገርኩት አሁንም ቢሆን አይለይልኝም ወዴትም መምጣትና መሄድ አያስፈልገኝም በኪነ ጥበብ ውስጥ ያለው*

ታማኝ ነው ዛሬም ያለው።

**ጥላ:-** ታማኝ በጣም ፈሪሃ እግዚያብሄር ያለው ሰው ነው ፖለቲካ አያምርበትም።እምነቱን ቢያጠብቅ ይሻላል ለሚሉህ ወገኖች ምን ትላቸዋለህ?

**ታማኝ:-** በእርግጥ በጣም በእግዚያብሄር የማምን እግዚያብሄር ሁሉን ማድረግ እንደሚችል የማምን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ነኝ።ትክክል ነው ፈሪሃ እግዚያብሄር ያለኝ ነኝ።እዚህ ላይ አልተሳሳቱም።ይህን ትቶ የሚባለው እኔ እምነቴን ያላላሁበት ጊዜ የለም።እግዚያብሄርም ከተጎዱ ሰዎች ጎን ይቆማል።እግዚያብሄር በእሱ አምሳል ፈጥሮን እኩል አድርጎ ፈጥሮን በዓለም ላይ የመጨረሻ ለማኞችና ድሆች ሆነናል።ይህን ትተን በእግዚያብሄር እንደበቅ ነው የምንለው?እግዚያብሄር እኮ ኢትዮጵያን የተሻለ አገር አድርጎ መገንባት የሚችል አዕምሮ ያለው ሰው ፈጥሯል።ግን ባንፃሩ የዓለም ደሃ ሆነናል።ስለዚህ ከሃይማኖት ሸፋን ወጥተን በትክክል በነፃነት የምንንቀሳቀስበትን ትግል ማድረግ ነው የሚገባን።እግዚያብሄር የፈጠረውን አንድ ጥጋበኛ ካድሬና ወታደር ሲገድለው ዝም ማለት ተገቢም አይደለም ወንጀል ሲፈፀም ዝም ማለት በእግዚያብሄርም በምድራዊውም ዓለም ያስጠይቃልና።ስለዚህ እምነቴንም አጥብቄ ለሰዎች ልጆች መብት መከበር እየሰራሁ እንዳለ ነው የማምነው።

**ጥላ:-** አሁን በኢትዮጵያ ባለው ስርዓት ላይ ያለህ አቋም ምንድን ነው?




**ታማኝ:-** እኔ አቋሜ ግልፅ ነው።አሁን ባገሪቱ ባለው ቡድን አገዛዝ ኢትዮጵያ የሁላችን አገር አይደለችም።ኢትዮጵያ ሁሉም ዜጎች በእኩልነት የሚኖሩባት አይደለችም።ዛሬ ህወሃት የሚባል ቡድን ኢኮኖሚውን ወታደሩን ንግዱን ተቆጣጥሮት ይገኛል።በተለይ ከምርጫ 97 በፊት በአንፃራዊ የነበረው ዴሞክራሲ ተሟጦ ተዳፍኗል።ኢትዮጵያውያን ከሁሉም የአፍሪካ አገሮች በታች ሆነናል።ለምሳሌ ያህል በኢንተርኔት ከሶማሊያ በታች፤በጋዜጣና በራዲዮ ከኬንያ በታች ነን ጭራሽ የገደለ የማይጠየቅበት ህወሃት የሚዳኝበት አገር እስከሆነ ድረስ ይህ ስርዓት ማብቃት አለበት የሚል ነው የእኔ አቋም።

**ጥላ:-** ገና ኢህአዴግ አ/አ ሲገባ ግንቦት 20/1983 ዓ.ም ነው ስርዓቱን በጦር መሳሪያ የሚገዛ ብለህ ለ CNN የገለፅከው በወቅቱ ምን ታይቶህ ነው?ትንቢት የመናገር ተሰጥኦ አለህ እንዴ?

**ታማኝ:-** ረጅም ሳቅ… ትንቢት እኮ አይደለም።የእነሱን ራዲዮ ከመግባታቸው በፊት እከታተል እሰማ ነበር።አንደኛ አንድን ህዝብ እንደ ህዝብ እናጠፋለን ብለው ነበር የተነሱት ያ ትክክል አይደለም።ሁለተኛ ለኢትዮጵያ ያላቸው ራዕይ የተሳሳተ ነበር መንገዳቸው በአጠቃላይ ጨለማ ስለነበር እንዳልከው በዛን ቀን ይሄ ቡድን እንደማይጠቅም ተናግሬያለሁ።ሰበካቸውን ቀድሜ አድምጬ ነው እዛ ድምዳሜ ላይ የደረስኩት።

**ጥላ:-** በቀድሞው ሰራዊታችን ማቋቋሚያ የስታዲየም ፕሮግራም ላይ እንዲሁም በአድዋ 100ኛ ዓመት በዓል ዝግጅትና በመሳሰሉት ክስተቶች ላይ ከሌላው ወጣና ድፍረት የተሞላበት ተቃውሞና ንግግር ስታደርግ እርምጃ ይወስዱብኛል ብለህ ስጋት ገብቶህ አያውቅም?

**ታማኝ:-** ስጋት ሊኖር ይችላል ግን በፍፁም በዛ ዘመን በዛ ሁኔታ እኔ ባደኩባት ኢትዮጵያ የአገራችን መሰረት የሆኑት ታሪኳ የነፃነት ተጋድሎዋ አርበኞቿ የሞቱላት ሰንደቅ ዓላማዋ እነዚህ በሙሉ እንደ ቆሻሻ በአንዴ በህወሃት ካድሬዎች ሲዋረዱ ከማየት ሞት ምንም አልነበረም።እሞታለሁ እንዲህ ያደርጉኛል ብዬ አስቤ አላውቅም።አሁን ተመልሰህ ስታየው ምናልባት የተለየ ግንዛቤ ይኖረኝ ይሆናል።ነገር ግን በወቅቱ አቅሜ የፈቀደውን ማድረግ እንደሚገባኝ ነበር የማስበው።

**ጥላ:-** ታማኝ ለትግራይ ተወላጆች ጥላቻ አለው ብለው ለሚያምኑ ወይም ለተሳሳቱ ሰዎች መልዕክትህ ምንድን ነው?

**ታማኝ:-** ጥሩ ጥያቄ ነው ያነሳኸው።ይህን ብዙ ጊዜ ተናግሬአለሁ።እኔ ከማንም በላይ የማምነው እራሴን ብቻ ነው።በማንም ላይ ጥላቻ የለኝም።በምን መነሻ ነው የትግራይን ህዝብ በጥላቻ የምፈርጀው።በተለይ ወጣቱ ተመራምሮ ፈትሾ እውነት ነው አይደለም የሚለውን መረዳት ሲችል አንድ ካድሬ ተነስቶ ታማኝ የትግራይ ተወላጆችን ይጠላል ሲለው ሊቀበለው አይገባም።ሰው ለምን ተገደለ ስትል ለትግራይ ህዝብ ካለው ጥላቻ ነው ማለት በምን ሳይንስ ይለካል? በምርጫ 97 ነብዩ የሚባል የ14 ዓመት ልጅ ተገደለ ይህ ለምን ይሆናል ስትል የስርዓቱ ፕሮፓጋንዲስቶች ትግራይን ስለሚጠላ ነው ብለው የሚያስተላልፉትን መልዕክት ህብረተሰቡ ጠንቅቆ ሊያውቅ ይገባል።ህወሃት የትግራይን ህዝብ ይወክላል ብዬ አላምንም።የህወሃትን ግፍ አስታኮ የትግራይን ህዝብ በጠላትነት መፈረጅ ትክክል ካለመሆኑም በላይ

ወንጀል ነው ብዬ የማምን ሰው ነኝ።አይደለም ለትግራይ ህዝብ ለመለስ ዜናዊም ቢሆን የግል ጥላቻ የለኝም ለፈፀሙት ወንጀል በህግ ይጠየቁ ከሚል እንጂ የግል ጥላቻ ስላለኝ አይደለም።ህወሃት የሚባለው ቡድን ውስጥ ብዙ ወንጀል አለ ማለትና ህወሃት ወንጀሉን በትግራይ ህዝብ ሽፋን ደብቆ ለማለፍ የሚጠቀምበትን ስልት ነጣጥሎ ማየት ይገባል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ላለ ዜጋ ሁሉ እኩል ፍቅር አለኝ።በመለስ ዜናዊ በሚመራው የህወሃት ቡድን ውስጥ ከፍተኛ ወንጀል እንዳለ ማስረጃው በእጄ ስለሚገኝ በህወሃት ላይ ገና ብዙ እናገራለሁ።ህወሃትንና የትግራይን ህዝብ ልዩነት ጠንቅቄም እገነዘባለሁ።

**ጥላ፡-** መለስ የመሬት መሸጥ መለወጥ በአገሪቱ የሚኖረው በኢህአዴግ መቃብር ላይ ብቻ ነው ካሉ በሁዋላ አሁን ለውጭ ኢንቬስተሮች መሬት መቸብቸባቸውን እንዴት አየኸው?ምንስ ጉዳት አለው?

**ታማኝ፡-** ጉዳቱን ከእኔ ይልቅ የሙያው ባለቤቶች ቢመልሱት መልካም ነበር።አሁን ይህንን ኢንተርቪው በምናደርግበት ወቅት እንኳን ኢትዮጵያውያን ይህ የእናንተ መሬት አይደለም ከአካባቢያችን ውጡ እየተባለ ህፃናት ነፍስ ጡር ሳይቀሩ በግፍ በወታደር ካደጉበትና እትብታቸው ከተቀበረበት ቦታ እየተፈናቀሉ ነው።በሌላ በኩል ግን ኢህአዴግ ለቱርክ ለህንድ ለፓኪስታን ለሳውዲ አረቢያና ለመሳሰሉት መሬት እየሸጠ ነው።

ከዛም በላይ ግን የሚያሳዝነው መሬት ላራሹ ብለው ህይወታቸውን ያጡት የኢትዮጵያ ውድ ልጆች ትግል መና መቅረቱ ነው።የእኛ አርሶአደሮች በልተው ማደር እያቃታቸው ሌላ ባለሃብት ከውጭ አምጥተው እህሉን ወደ ውጭ ለገበያ እንዲያቀርቡም መፍቀዳቸው አስገራሚ ነው።

ከዚምባብዌ ብዙ መማር ይቻላል።የዚምባብዌ መንግስት መሬት ከነጮቹ ቀምቶ ለጥቁሮቹ በመስጠቱ የደረሰበትን የኢኮኖሚ ማዕቀብ እያየን ነው።ህወሃት ወቅቱን ጠብቆ አገሪቱን የሚያተራምስ ድግስ ነው ከወዲሁ እየደገሰልን ያለው።አንድ ዜጋ በአገሩ በራሱ መሬት መብት አጥቶ እየተፈናቀለ በምን መለኪያ ነው ፍትሃዊ ነው የሚባለው።ስለዚህ የመለስ የራሳቸው ምላስ እርስ በራሱ የሚጣረስ ከመሆኑ



በላይ ውጤቱ ከፍተኛ አደጋን የሚያስከትል ይሆናል።

**ጥላ፡-** የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ቱኒዝያውያን ግብፃውያን ሊቢያውያንና ሶሪያውያን መሆን ያልቻለበት ምክንያት ምንድን ነው ትላለህ ?

**ታማኝ፡-** የህወሃት ትኩስ ዱላ ከ7 ዓመታት ወዲህ(ከምርጫ 97 በሁዋላ) ነው እየበረታ የመጣው።ቅንጅትና ህብረትም ህዝቡ የሰጣቸውን ድምፅ በአግባቡ ስላልተጠቀሙበት ያመናቸው መሪዎቹም በተለያዩ ምክንያቶች ስለተንሸራተቱ ብሎም በአገሪቱ ውስጥ ተምረህ ስራ ለማግኘት እንኳን የኢህአዴግ አባል መሆን አለብህ የሚለው አሰራር 5 ለ 1 የሚባለው መዋቅር ሁሉንም በአንድ አስሮ የመምራት ሁኔታ መፈጠራቸው ለጊዜው ሰው በጥርጣሬ እንዲተያይ ስላደረገው ነው።አሁን ግን ሁኔታዎች እየተለወጡ ነው።ኢትዮጵያዊው ሞሃመድ ቦአዚዝ የኔሰው ገብሬ አይሞከርም የተባለውን ትግል ራሱን በማቃጠል ችቦውን ለኩሶታል የታላቁ ሩጫ ወጣቶች ድምፅ እየተበራከተ ነው ከሙስሊሙ ጋር ህወሃት የፈጠረው ውዝግብ ለስኳር ፋብሪካ በሚል ታሪካዊና ቅዱስ ቦታዎችን በመድፈር መምህራንን ደሞዝ ጭማሪ በሚል በክብራቸው ላይ ማላገጡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ወደ አንድ አቅጣጫ እያመሩ ነው።ህወሃት የሚባለው ቡድን ተፈጥሮው ከማንም ጋር መስማማት የማይችል ነው።

በአጠቃላይ አንድ በሽተኛ ወደ ሃኪም ቤት ሲመጣ ሃኪሞች መጀመሪያ ትኩሳቱን ነው የሚለኩት በሽተኛው ትኩሳቱ ሃይለኛ ከሆነ ከፍተኛ ችግር እንዳለበት ያውቃሉ።ከዛ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳሉ።በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ከፍተኛ ትኩሳት የሚታይባት አገር እየሆነች ነው።ይሄ ትኩሳት ታዲያ የዓረቡን ዓለም ህዝባዊ ማዕበል ወይም ሌላም ነገር ሊያመጣ ይችላል።መቼ የሚለውን እኔ መናገር አልችልም።ግን የማይቀር ነገር ነው።

**ጥላ፡-** ማክረር ለማንም አይበጅም የሚል አቋም አለህ።በአክራሪነት ጎራ ያሉ የተቃዋሚውም ሆኑ የደጋፊ ሃይሎች ምን ይጠበቅባቸዋል?

**ታማኝ፡-** ማክረር በየትኛውም መልኩ ተገቢ አይደለም።በፍቅር ጓደኛሞች መካከልም ቢሆን ማክረር አግባብነት የለውም።ይህ ሁኔታ ነገሮች ባልተሳኩ ጊዜ ራስን ወደ መሳት መጣል መጉዳት ነው የሚያደርስህ።በሃይማኖት ማክረርን ካየን ካንተ እምነት የእኔ ይበልጣል ወይም ያንተ ያነሰ ነው ማለት ነው፡፤ይሄ ደግሞ በፍፁም ስህተት ነው።በዘርም ብትሄድ አንዱን አልወድም ያንን እንቃለሁ ልትል ነው ይሄም በጭራሽ አያስኬድም።

በማክረር ውጤት ያመጡ አገሮች አላውቅም።በመቻቻል ግን አውሮፓና አሜሪካን ለአብነት መውሰድ ይቻላል።ደቡብ አፍሪካውያን ከዘር መድሎና ከፖለቲካዊ የዘር ልዩነት የወጡት መቻቻልን በመምረጣቸው ነው።በተለይ በዘር ፍቅር መስከርና ማክረር ሞት አደጋና መጠፋፋትን ነው የሚያስከትለው።በእኛም አገር “መቻቻል ይቻላል“የምትል መፈክር አለችኝ።መቻቻል ፍሬዋ ያማረና መልካም

ነው።ለዚህ ነው በአክራሪነት ጎራ ያሉትን ሁሉ አያዋጣችሁም ተቻችለን እንኑር የሚል መልዕክቴን የማስተላልፈው።

**ጥላ፡-** ግንቦት 7 እና ኦነግ የጀመሩት መግባባት ሌሎቹንም ሃይሎች እንዲያካትት ምን መልዕክት አለህ?

***ታማኝ፡-*** ጥሩ አንስተሸዋል።እኔ ኦነግም ሆነ ግንቦት 7 ተነሳሽነቱን ወስደው መወያየታቸው ተገቢም ነው ትክክልም ነው እላለሁ።ኢትዮጵያዊ አይደለሁም ከሚለው ጎራ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል አንድ ሰውም



ቢሆን መምጣቱን በበጎ ነው የማየው።ኢትዮጵያዊ የአንድነት ሃይሎች ማን እንዲያካትታቸው ነው የሚጠብቁት? ማነው የሚጠራቸው?ማን እንዲሰበስባቸው ነው የሚፈልጉት?ህዝቡ እኮ ና ሲሉት ይመጣል አንጣ ሲሉት ይሰጣል እኔ የምለው ማንንም አትጠብቁ በኢትዮጵያ እኩልነትና አንድነት የምታምኑ ከሆነ i am willing to discuss with you ብላችሁ ከዛሬው ተጠራሩ ነው።አንዱ ጠሪ ሌላው ተጠሪ መሆን የለበትም።ኦነግም ሆነ ግንቦት 7 የምትጮሁለትን ህዝብ ሸክሙን ገና አላቃለላችሁለትም ሸክሙን ለማቃለል ጊዜው ሳይሄድ ከሌሎቹም ሃይሎች ጋር ተደዋወሉ ተጠራሩ ቁጭ በሉና ተወያዩ ነው መልዕክቴ።

**ጥላ፡-** ኢትዮጵያውያን በጋራ ተቻችለን መሄድ የሚገባን ወቅት አሁን እንደሆነም በመስበክ ላይ ትገኛለህ።ይህ ወቅት ወሳኝ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?

***ታማኝ፡-*** ሰሞኑን በደቡብ ክልል እንደተከሰተው ያለአካባቢህ መጣህ እየተባለ አንዱ አንዱን ህዝብ ማባረር የለበትም።ሰሜኑ የደቡቡን ደቡቡ የሰሜኑን ማባረር የለበትም።ይህ አይነቱ ፖለቲካ አገራችንን ያተራምሳል።እንአከሌ መፍትሄ ያመጡ ይሆናል ተብሎ ዳር ላይ የመቆም አስተሳሰብ ሊሰበር ይገባል።የኦሎምፒክን ምሳሌ ልንገርህ እነ ሃይሌ ቀነኒሳ ደራርቱ ሲሮጡ እኛ ቁጭ ብለን እንመለከታለን።እነሱ ሯጭ እኛ ተመልካች ነንና።በኢትዮጵያ ፖለቲካ ግን አትሌትና ተመልካች የለም።ሁላችንም አትሌት መሆን ነው ያለብን።አንዱ ሯጭ ሌላው ተመልካች እዚህ ጋር አይሰራም።ሁላችንም በጋራ ተሳትፎ አትሌቶች ነው መሆን ያለብን።ያን ካደረግን ለውጥ ይመጣል።ካልሆነና ከዘገየን ግን አገራችን ላይ አደጋ እየጋበዝን ነው።

ዳር ሆኖ እንደ ሲኒማ በማየት ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ አይመጣም።በተለይ በውጭ አገር የሚገኘው ህዝብ እሱ ያገኘውን ነፃነት ቤተሰቦቹም በአገር ቤት ሊያገኙ ይገባል።እያንዳንዳችን የምንችላትን አስተዋፅኦ ማድረግ ይገባናል ነው የምለው።

**ጥላ፡-** እንደ አክቲቪስትነትህ አሁን ያለው የኢህአዴግ ስርዓት ቢወገድ ሊተካው የሚችል ሃይል አለ ብለህ ታምናለህ?

***ታማኝ፡-*** በሚገባ አለ!ኢህአዴግን ለመተካት የሚያስችል ሃይል አለ። በደንብ አለ።እነ መለስና መሰሎቻቸው እንኳን ኢትዮጵያን መርተዋታል።ኢህአዴግ እኔ ከሌለሁ አገሪቱ ዋጋ የላትም በማለት እንዲፈራ የሚያደርገው ስልት ነው ይሄ።በቂ የሰው ሃይል በቂ ዕውቀት ያላቸው ኢትዮጵያውያን አሉ።በአገር ውስጥም በውጭም። በአግባቡ ካስተካከልነው ያለምንም ተኩስና ረብሻ ሽግግር መፍጠር እንችላለን።ከተሰራ አስፈላጊው የሰው ሃይልና ድርጅትም አለ።

**ጥላ፡-** ኢህአዴግን ለማስወገድ መፍትሄው ምንድን ነው ትላለህ?

***ታማኝ፡-*** ህወሃት/ኢህአዴግን ለማስወገድ 1ኛ/ የመጀመሪያው መፍትሄ ፍርሃትን መስበር ነው።የእነሱ ዋነኛው የዕድሜያቸው ማራዘሚያ ፍርሃትን ማስረፅ ነው። ስብሰባም ስንሄድ እንድንፈራ ያዩናል ብለን ያውም በውጭ አገር በአገር ቤትም ተመሳሳይ ነው።ትምህርትህን ተምረህ ስራ ማግኘት መብት መሆን ሲገባው ኢህአዴግ ካልሆንክ የሚል መስፈርት ምን የሚሉት ነው።ቢሆንም እነዚህም ፍርሃቶች መሰበር አለባቸው። 2ኛ/ እኛ አያገባንም አይመለከተንም ከሚል ስሜት ወጥተን ያገባናል ይመለከተናል ማለት መቻል አለብን።የእኔ አስተዋፅኦ እርባና አለው ብለን ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ አለብን። 3ኛ/ **ESAT** በዓረብ ሳት ወይም በሌላ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሶስት ተከታታይ ወራት ማሰራጨት የሚቻልበት ሁኔታ ቢመቻች ኢህአዴግ አንድ ሌሊት አያድርም።ይህ ባይሆን እራሴን ከፖለቲካው አገላለሁ።ህብረተሰቡም በምንም መልኩ ከማህበራዊ ህይወታችን ያግለኝ ብዬ ወስኛለሁ።

አንዳንዶቻችን በ60/70 ዎቹ እንደነበረው ታንክ ግዙፍ ሰራዊት ይዞ ይመስለዋል።ህዝብ በራሱ ተነሳሽነት መንግስትን እንደሚገለብጥ እያየን ነው።ህወሃት በአየር ላይ የተንሳፈፈ ቡድን ነው።ህዝባዊ መሰረት ስለሌለው ለማስወገዱ ብዙ የሚከብድ አይሆንም።

**ጥላ፡-** የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናት አንተ ላይ እያነጣጠሩ የመጡበት ምክንያት ምንድን ነው?

***ታማኝ፡-*** ይህን ጥያቄ እንኳን አነጣጣሪዎቹ ቢመልሱት የተሻለ ነበር።ነገር ግን ይመስለኛል የአኬልዳማ ድራማቸው እንዳልሆነ ሆኖ ከተሰበረ በሁዋላ ወደ እኔ ጣት መቀሰር ጀምረዋል። እኔ እውነት ናቸው የምላቸውን ነገሮች እንደው ለዲስኩር ሳይሆን በማስረጃ አስደግፌ ነው የማቀርበው።እነሱ ለምን በኔ ላይ ማነጣጠር እንደጀመሩ ግን እኔ ስለራሴ ከምናገር ይልቅ ሌላው ቢመልሰው ይሻላል።

**ጥላ፡-** እንደ ጥላ መፅሄት እምነት ግን የምታነሳቸው ሃሳቦች ተደማጭነት እያገኙ መምጣታቸውና በባለስልጣናቱ ሰፈር እረፍት መንሳትህ ይሆናል።

***ታማኝ፡-*** ከእኔ እና ከህወሃት ውጭ ያለው ሰው ስላነሳኸው ጉዳይ የተሻለ መናገር እንደሚችል አምናለሁ።

**ጥላ፡-** ለአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ኮሎኔል በዛብህ ጴጥሮስን አስመልክተህ ያቀረብከው ከእስር ልቀቁልን ጥያቄ ከምን ደረሰልህ?

***ታማኝ፡-*** ጥያቄዬን በህዝብ ድጋፍ

ለማረጋገጥ የሚያስችለኝን የድጋፍ ፊርማ በተለያዩ ከተሞች እየተዘዋወርኩ እያሰባሰብኩ ነው።ጥያቄውን ካነሳኸው



አይቀር አንዳንድ ሰዎች ቃል ተገብቶልሃል ወይ? ያገኘኸው መልካም ዜና አለ ወይ እያሉ ስልክ በመደወል ጭምር እየጠየቁኝ ነው።እዚህ ላይ ግልፅ ለማድረግ እኔ ምንም የተገባልኝ ቃል የለም ምንም ነገር አነሳስቶኝም አይደለም።የኮሎኔሉ በተለያዩ ጊዜያት ከ20 ዓመታት ያላነሰ መታሰር፤ህወሃትም በቀይ መስቀልም ይሁን በሌላ መንገድ ኮሎኔል በዛብህን እንደማግኘት ዕቃ እንኳን እንደጠፋበት ሰው ሳይቆጥር ዝም ማለቱ በሰብዓዊነት ሃዘኔታ ገብቶኝ እንጂ ሌላ እንዳልሆነ ግልፅ ማድረግ እፈልጋለሁ። የኤርትራው ፕሬዚዳንትም ጥያቄው ምንም ዓይነት የፖለቲካ መነሻ የሌለውና ከሰብዓዊነት በመነሳት አባት ልጁን ለማየት ካለው ጉጉት አኳያ ብቻ ተመልክተው በጎ ምላሽ እንደሚሰጡኝ በመተማመን በቅርቡ የህዝብ ድጋፉን ከደብዳቤ ጋር በማያያዝ ዋሽንግተን ዲሲ ለሚገኘው የኤርትራ ኤምባሲ አቀርባለሁ።ውጤቱንም ተከታትዬ ለህዝቡ ይፋ አደርጋለሁ።

**ጥላ፡-** ከ7 ዓመታት በፊት አንድ የቀልድና የቁም ነገር DVD ኮሜዲ ለእይታ አቅርበህ ነበር Creativity ህን ብዙ ሰው አድንቆልሃል።ከዛ ፖለቲካው ሳበህ መሰለኝ ከአርቱ ዓለም እየራቅህ ነው።በቅርቡ ያሰብከው ነገር የለም?

**ታማኝ፡-** ጠፋህ ሊሆን ይችላል።እንዳልከው በዘፈን መድረኮች ላይ ብዙ አልታይም።እንዳልከው ትኩረቴን የሳበው የአገሪቱ ጉዳይ ነው።በርካታ ሰዎችም ተመሳሳይ ጥያቄ እየጠየቁኝ ነው።እስቲ ትንሽ ጊዜ ወስጄ አየዋለሁ።እኔ ከአርቱ መነጠል አልችልም።የአገሪቱ ጉዳይ መስመር ይዞ የምወደውን ሙያዬን በሙሉ ልቤ በነፃነት መስራት ነው የምፈልገው።

**ጥላ፡-** ስለዚህ እንደምንም ጊዜህንም አጣበህ ቢሆን በአዲስ የጥበብ ስራ እንደምንገናኝ ቃል እየገባህልን ነው።እንጠብቅሃለን። **ታማኝ፡-** እሺ እስቲ እሞክራለሁ።

**ጥላ፡-** እኔ ጥያቄዬን ጨርሻለሁ።መልዕክት ለማስተላለፍ ግን ዕድሉን ሰጥቼሃለሁ።

**ታማኝ፡-** የእኔ መልዕክት እኔ ምን አቅም አለኝ የሚል የመሸነፍ ስሜት ከኢትዮጵያውያን መወገድ አለበት።እኔ የኖርኩበት የጥበብ መድረክ ነው።በጥበብ ስራ አውሮፓም አሜሪካም ስንቀሳቀስ ትራንስፖርቴ ተከፍሎ ሆቴል ተይዞልኝ መድረክ ላይ ስወጣ ተጨብጭቦልኝ ስወጣ ፊርምልኝ ተብዬ በጣም አልጋ ባልጋ ከሆነና ከተደላደለ ኑሮ ወጥቼ ነው የበኩሌን አስተዋፅኦ እያደረኩ ያለሁት።በአገራችን ነገ የሚኖረውን ነፃነት ናፍቄ ነው እንጂ ገንዘብ ተገኝቶበት አይደለም።ለሰው ልጆች መብት መቆም ታላቅ ክብር ነው።ይህንን ሃቅ ነው ህዝቡ ማወቅ ያለበት።በስንፍና አቅም የለኝም ብሎ ከመኖር የእኔም አስተዋፅኦ ለውጥ ያመጣል ብሎ ሁሉም ዜጋ እንዲያስብና ለተግባራዊነቱ እንዲረባረብ ነው አደራ የምለው።አመሰግናለሁ።

**ጥላ፡-** አክቲቪስት ታማኝ በየነ የመፅሄታችን ልዩ የክብር እንግዳ ሆነህ ሃሳብህን ስላካፈልከን በአንባቢዎቻችን ስም ከልብ እናመሰግናለን።ወደፊትም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሃሳብህን ስንሻ እንደምትተባበረን እናምናለን።



# የነበልባሉ ዘመን ይብቃን

**Abdi Mohammed Ali/Hilpoltstein**

አምባገነኑ የወያኔ ስርአት የግፍ አገዛዙን በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በመጫን አሠቃቂና ጭቋኝ ተግባራትን በመፈጸም ብሎም ህዝቡን እርስ በራሱ በዘር በመከፋፈልና ተዋደው ተከባብረው የሚኖሩትን ሃይማኖቶች በማመስና በማናጋት የእድገት፣ የሠላምና የብልጽግና ጸር ሆኗል፡፡

ከዚህ አሰቃቂና የጭቆና አገዛዝ ለመላቀቅ በየዘመኑ በየግዜው ዜጐች የፍትህ ጥያቄ ማንሳታቸው አልቀረም፡፡ ነገር ግን ጥያቄዎቻቸውን የወያኔ መንግስት በወንጀል እየፈረጀና አሸባሪ የሚል ስያሜ እየሰጠ በአይን ካልታየ በቀር ቢነገር የማይታመን የግፍ ቅጣት እየቀጣ እነሆ ለ21 ዓመታት ህዝቡ ላይ የልብ ቁስል እያስቀመጠ ተጉዟል፡፡

ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ አምባገነኑንና ዘረኛውን የወያኔን አገዛዝ በጋራ በመሆን መፋለም ይኖርብናል፡፡ የወያኔን አገዛዝ ማስወገድ ከቻልን ስደት፣ መድሎ፣ ጭቆናና የዘረኝነትን መርዝ ከሥራቸው በመንቀል መጪውን ዘመናት ብሩህና መልካም አስተዳደር፣ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች የሚከበሩበት፣ ሰላምና ፍትህ የሠፈነባትን ኢትዮጵያ መገንባት እንችላለን እያልኩ ሃሳቤን በዚሁ አበቃለሁ፡፡

# ወዴት እየሄድን ነው?

**Sisay Getachew /Vlotho**

የሰፊው ሕዝብ ብሶት ወለደኝ የሚለው ኢሕአዴግ በግንቦት ወር 1983 ዓ,ም ደርግ ትቶት የሄደውን አልጋ ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ከተቆጣጠረው በኋላ የሃገራችን ፖለቲካው አየር በውጥረት ተሞልቷል፡፡

ወዴት እየሄድን ነው አሁን የመንግስት ስልጣን የያዘው ኢሕአዴግ የታገለው ዘላለማዊ ስልጣን ይዞ ለመቆየት ነውን በየጊዜው ሲነገር የምንሰማው ለህዝቦች መብት ለዲሞክራሲ እና ለመልካም አስተዳደር ሳይሆን ለግል ጥቅም ነው ማለት ይቻላል፡፡

የከፍተኛ ተቋም /ዩንቨርስቲ/ ተማሪዎች እና ምሁራን የነገ ህዝብና ሃገር ተረካቢዎች ላይ እየደረሰ ያለው ኢ-ሠብአዊ በደል በገሃድ እየተለፈፈና የማን አለብኝነቱን እንቅስቃሴ እያስፋፋ እየታየ ነው፡፡ የመጻፍ፣ የመናገር የመቃወም የመደገፍ የመምረጥ ያለመምረጥ መብታችንን በማፈን በኢሕአዴግ ተቋዋሚዎች እንደ ጦር ካምፕ እየተጠበቁ ትምህርታቸውን በግድ እንዲቀጥሉ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ይህን የተቃወሙትን ተማሪዎችና የሕብረተሰብ ክፍል በማሰር በማንገላታት በመግደል እና አገር ጥለው እንዲሰደዱ በማድረግ ላይ ነው፡፡ ምሁራንና ተማሪዎች የማንም የምንም ሳይሆኑ የነገይቱ የኢትዮጵያን እና ሕብረተሰቡን ተረካቢዎች መሆናቸውን አጥብቆ መገንዘብ ሲገባ መርሳትና መዘንጋት የለበትም፡፡

የኢሕአዴግ አጋች እና ታጋች የአፈናው ድራማ አጥብቆ ካልተገታ ወዴት እየሄድን ነው በማለት ለአንድ አፍታ ቆም ብሎ ወደ ኋላ በመዞር ማተኮር ማስተዋል ይገባዋል፡፡ እየተሠነዘረ ያለው ቅጣት መልስ መጠየቅ ቂም ይዞ ምሁራንን እና ተማሪዎችን መቅጣት የብስራት ምልክትነት ሳይሆን የስሜታዊነት መገለጫ ምልክት ነው

# ታሪክን ለማጥፋት የተነሣ ስርዓት

**Eden Dawit Kidane /Gießen**

ከመነሻው ጀምሮ በዘር መድሎ የተለከፈው የወያኔ መንግስት አስተዳደር በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ግፍና መከራ በየአቅጣጫው እየጨመረ እና ይዞታውንም እያሠፋ ይታያል። ይህው አሁንም በየገጠሩ በሠላም ይኖር የነበረውን ሕዝብ በሠላም ግዜ ለስራም ሆነ ለተለያዩ ጉዳዬች በየክፍለ ሃገሩ እየተዘዋወረ ይሠራና ይኖር የነበረው ሕዝብ በወያኔ የአስተዳደር ብልሹነት የተነሣ የአለም ሕዝብ ለኑሮ ተስማሚው በሆነ ቦታ መኖር ይገባዋሉ በሚባልበት በአሁኑ ዘመን በኢትዮጵያ እየታየ ያለው አማራው ፣ ጋምቤላ ሄዶ ኦሮሞው ጐንደር ሄዶ የመኖርና በአገሩ ተዘዋውሮ የመስራት ህልውናው አደጋ ላይ ወድቋል፡፡ ለዚህም በቅርቡ በአማራው ብሄር ላይ የደረሰው የመፈናቀል ዜና ይህንን ብልሹ አስተዳደር የሚያጋልጥ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ከአባቶቻችን የወረስነው በጋራ የመኖርና የመረዳዳት ባህላችን ሲሆን ይህንን የመከባበር ባህላችንን ለማጥፋት አረመኔውና ጨፍጫፊው የወያኔ መንግስት የቅንጦት ህይወት ይሉኝታ ባሳጣቸው ባለስልጣናቶቹ ምክንያት ከመቼውም ጊዜ በላይ በመሯሯጥ ላይ ይገኛል። ታዲያ ይህንን ታሪክን ለማጥፋት ስርዓት በቃ የምለው መቼ ነው? ለህዝባችንስ አለንልህ የምንለው መቼ ነው? የኢትዮጵያ ልጆች ለሕዝባችን ልንደርስለት የሚገባን ዛሬ ነው ስቃይ በርትቶ እያለ ድምጽን ለአለም ማሠማት እንዴት ያቅተናል ይህንን አረመኔ በቃ እንበለው ለዚህም ትግላችን ኢሕአፓ ከጎናችን ነው። ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ፡፡

# ቅጥ ያጣው የወያኔ ትንኮሳ

**Yewondwsen Anagaw/ Hilpoltstein**

የወያኔ መረን ያጣ አምባገነናዊ አገዛዝ ህዝቡን እየገደለ፤ እያሰረ፤ እንዲሁም በተለያየ መንገድ እያሰቃየ በምርጫ ተሸንፎም እንኳን በሚቀልባቸው የአግአዚ ወታደሮች ታግዞ የቻለውን ያሕል ገድሎ ሌሎችን አስሮ ከሚኒሊክ ቤተመንግስት አልወጣም ብሎ ስልጣን ላይ እንደተንጠለጠለ 21 አመት አስቆጥሯል፡፡

ህዝቡ ከምርጫ 97 በሁዋላ

ዝምታን መርጦ የቆየ ቢሆንም ባሁኑ ጊዜ ከኑሮ ውድነቱ በተጨማሪ ቅጥ ያጣ የወያኔ ትንኮሳ ተጨምሮበት ህዝቡ መነቃነቅ ጀምሯል ባሁኑ ወቅት ወያኔ በተለያየ አጋጣሚ ህዝቡን እየተነኮሰው ነው፡፡

ለዚህም ከ22 ሺ በላይ የአማራ ህዝብ በዘሩ ተመርጦ ከደቡብ እየተፈናቀለ መሆኑ በዋልድባ ገዳም የቅዱሳን መቃብር ፋብሪካ እንገነባለን በሚል ሰበብ መታረሱ እንዲሁም ሌሎች ገዳማት ላይ እየደረሰ ያለው ቃጠሎና በርካታ ግፍ፤ በእስልምና ሃይማኖት ላይ የሚደረገው ጣልቃ ገብነት በሽብርተኛ ስም ንጹሃን ዜጐችን ወደ እስር ቤት ማጋዝ፤ እንዲሁም ሌሎች በርካታ ችግሮች ተጨማምረው ህዝቡን እያማረሩት መሆኑ በቂ ማስረጃ ነው፡፡

ወያኔ በተደጋጋሚ የሚያደርገው ትንኮሳ ዙርያውን ተወጥሮ ፍርሃት ውስጥ ለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ ይሆነናል። በመሆኑም ባገር ቤትም በውጭም ትግሉ ተቀጣጥሎ መቀጠሉ አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝበን በያለንበት ይህን አምባገነን ስርአት ለመገርሰስ ተባብረን እንታገል፡፡ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

# ኧረ ወገን! ምን እስክንደረግ ነው የምንጠብቀው?

Woineshet Sitotaw/Heusenstamm

በአሁኑ ሰዓት ሰብአዊ መብቶቻቸው ተነፍገው በሳውዲአረብያ እስር ቤት በመማቀቅ ላይ የሚገኙ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን በህዝባችን ላይ እየደረሰ ያለውን ግፍና በደል ከማየት ሞቱን መርጦ የገዛ ስጋውን አቃጥሎ ህይወቱን ለነጻነት የሰዋው ምርጥ ወንድማችን የኔሰው ገብሬ፣ እንደሰው ልጅ ሳይሆን እንደ ዶሮ የፈላ ውሃ ተለቆባት በህይወቷ እያለች ስጋዋ ከላይዋ ላይ ተሞሽልቆ ሲረግፍ በአይና እንድታይ ጭካኔ የተሞላበት ግፍ ደርሶበት ከሞት የተረፈችው እህታችን ሸዋየ፣ በግብጽ በረሃ ተይዘው 13,000 ዶላር ካላመጣችሁ ኩላሊታችሁን እንወስዳለን የሚባሉት በቤሩት ከፎቅ እየተወረወሩ የሚሞቱት በየመን ቀይ ባሕር ውስጥ ያለቁትን ብዛት ቤት ይቁጠረው። ይሕ ሁሉ ሲሆን ግን ከደሀ ገንዘብ ህዝብ በሰበሰበው ገንዘብ የቅንጦት ሕይወት የሚኖረው አምባገነኑ የወያኔ መንግስት አንድም ቀን ለምን ብሎ ለዜጐቹ ተቆርቁሮ አያውቅም፡፡

ግን ለምን? ይህ ሁሉ እየሆነ ያለው ለሁሉም ዜጐች እኩል የሆነ የትምህርትና የምጣኔ ሃብት ክፍፍል ባለመኖሩና የፖለቲካ ነጻነት መታፈን ከፍተኛ የሆነ ሙሰኝነት በመስፋፋቱ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

አምባገነኑ የወያኔ መንግስት የዜጐቻችንን ችግር ስቃይና ሞት ከቁብ ሳይቆጥር ይባስ ብሎ ሰው በዘሩና በፖለቲካዊ አመለካከቱ የሚደርስበት ግፍ፣ በደል፣ እስራትና ሞት ተባብሶ ቀጥሏል፡፡ ከ30 ዓመት በላይ በህጋዊ መንግስት በሰፈራ ከኖሩበት ደቡብ ኢትዮጵያ ከ70,000 በላይ የአማራ ተወላጆችን እንደ ባእድ "ወደ ሃገራችሁ ተመለሱ" ተብለው ሐብትና ንብረታቸውን ትተው እንዲወጡ ያደረገ ዘረኛው መንግስት ወያኔ እኛ ኢትዮጵያውያን ስደታችን በውጭ ሃገራት ብቻ ሳይሆን በሃገራችንም እንዲሆን አድርጓል፡፡

አምባገነኑ የወያኔ መንግስት ኢትዮጵያ የምትባል ሃገር እንዳትኖር ቆርጦ የተነሣ እውነተኛ የኢትዮጵያ ጠላት ለመሆኑ 21 ዓመት ሙሉ የሰራው የዘረኝነትና የመበታተን ስራ በቂ ማስረጃ ነው፡፡

ታዲያ ይሕንን አምባገነን መሪ እስከመቼ ነው የምንታገሰው? በቃ!!! ግዜው አሁን ነው ይሕንን ግፍና ሰቆቃ ከምንጩ ለማምከን እኛ ኢትዮጵያውያን ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ወያኔን ለማስወገድ በጋራ መነሳት አለብን፡፡ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

# ዴሞክራሲ ለማን?

Helen Tesfay Kebede /Staufenberg

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትላንት በፊውዳል ገዢዎች ሲገዛና ሲረገጥ ንጉሶቹ እራሳቸውን ከአምላክ ተሾመውና ተቀብተው ሕዝብን እንደሚያስተዳድሩ የማይቀሩና የማይለወጡ ለዘላለም ገዢዎች ሆነው ቀርበው ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በትግሉ ከጫንቃው አውርዶ ጥሏቸዋል፡፡

በጊዜው ግን ተደራጅቶ ስልጣኑን የሚረከብ የተደራጀ ድርጅት ባለመኖሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደሙን የከፈለበት አብዮት በወታደሮች እጅ ገብቶ ሕዝቡን መጨፍጨፍና መግዛት ጀመረ፡፡ ኮምኒስት ነኝ ሶሻሊስት ነኝ ይል የነበረው የደርግ መንግስት ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጆችን አርዷል ገሏል ከዛም አልፎ የገደላቸውን ዜጐች ሬሳ በገንዘብ ለቤተሰቦቻቸው ሸጧል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በጠንካራው ትግሉ አሁንም ታግሎ ይሄንን ፋሽስታዊ ስርአት ከስሩ ገርስሶ ጥሏል፡፡

አሁን ደግሞ ያላለፈለት የኢትዮጵያ ሕዝብ የውሸት የዲሞክራሲ ልብስ ለብሶ የመጣውን የኢሕአዴግን መንግስት ማለት የመለስ ዜናዊን መንግስት እየተጋፈጠው ነው፡፡ ይሕ የበግ አጐዛ ተሸፍኖ የመጣውን ተኩላ ሕዝቡን ዲሞክራሲ አለሕ ቢለውም ዲሞክራሲው ለተወሰኑ የገቺ ክፍሎች ብቻ እንደሆነ በደንብ ተገንዝቦታል፡፡

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርሶ የማይበላበት ነግዶ የማያድርበት ሃገር በዲሞክራሲ ስም ተሸፍኖ እንደ ኮሶ እየመረረው እንዲቀበለው በግድ ደግሞ ይሄን ዘረኛ መንግስት እንዲቀበለው ወያኔና የሱ አጋዥ በሆኑት መንግስታት እያስገደዱት ነው፡፡

የወያኔ መንግስት በዲሞክራሲ ስም የኢትዮጵያን ሕዝብ ባሕል አንድነት ተሳስቦ የመኖር በየሐይማኖቱ ተከባብሮ የመኖር ልምዱን እያጠፋበት ነው፡፡ትናንትና የጋምቤላ ሕዝብ፣ ዛሬ

ደግሞ የሶማሌ ሕዝብ በኦጋዴን አካባቢ በዲሞክራሲ ስም እየተጠፈጠፈና እያለቀሰ ነው፡፡ይሄን ጥፍጠፋ ሊመሰክሩ የገቡ የስዊድን ጋዜጠኞችን እያሰቃየ ነው ኧረ ስንቱ ይዘርዘር ለመሆኑ ይሕ ዲሞክራሲ ለማነው?

የኢትዮየጵያ ሕዝብ ግን ይሄን አውቆ ድሮ እየታገለው ነው አንድ ቀን ደግሞ እንዳለፉት ስርአቶች ተገርስሶ ይጣልና እውነተኛው የሕዝብ ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ይሰፍናል፡፡

# በዘር የተከፋፈለ የወያኔ ዲሞክራሲ

**Yohannes Samson /Badhersfeld**

ያለፉት የሀገራችን ገዥዎች ኢትዮጵያን አንድነቷን በመጠበቅ አሁን ላለው ለዘረኛው መንግስት ለወያኔ አስረክበው ነበር፡፡ ነገር ግን ገና እግሩ እንደረገጠ ነበር ሀገር መገነጣጠል የጀመረው፡፡ ለምሳሌ ብንወስድ ከ20 አመት በፊት ኤርትራ እንድትገነጠል ለማመቻቸት ፈር የቀደደው ወያኔ ነው፡፡ ታዲያ ይህን የሰሙ አንዳንድ የሀገራችን ክልሎች የመገንጠል ጥያቄ በማቅረብ ላይ ይገኛሉ፡፡

ወያኔ ያ ያለፈው ስህተት አልበቃ ብሎት በተደጋጋሚ አሁንም ጥፋቶችን በመስራት ላይ ይገኛል፡፡ ሌላ ምሳሌ ብንወስድ አሁን እየተደረገ ያለ አንድ ብሄሩ አማራ የሆነ ልጅ ኦሮሚያ ውስጥ ተወልዶ አድጎ ባህሉን ወጉን እንዳለ አብሮት ያለው እዛው የተወለደበት ክልል ሆኖ ሳለ ባገኘው ትምህርት እውቀት ተዋደድሮ ለመስራት እውቀቱ እያለው ኦሮሚያ ወይም እዛው የተወለደበት ክልል ውስጥ ተወዳድሮ መቀጠር አይችልም፡፡ እሱ ኦሮሞ አይደለማ፡፡ ሌላውም ክልል ልክ እንደዛው። ይሕ ሁሉ የወያኔ ስራ ነው፡፡ በተጨማሪ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ተመርቆ ስራ ለማግኘት ተማሪ ሳለ የወያኔ ፓርቲ አባል መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ይባስ ብሎ ለህዝብ አገልግሎት የተቋቋሙ ባንኮች ኢንሹራንሶች እንኳን ከስማቸው አንስቶ በዘር የተከፋፈሉ ናቸው፡፡

ታዲያ ወያኔ ይህ ህዝብ እርስ በእርስ ሲጋጭ ምን ይሆን ደስታው አሜሪካውያን 52 ግዛቶችን ይዞ በአንድ ቋንቋ አንድ ሀገር አድርጋ አለምን በሚያስገርም ሁኔታ ነጻ በሆነ ዲሞክራሲ በከፍተኛ እድገት ለአለም ህዝብ ምሳሌ ሆነዋል፡፡ ታዲያ በወያኔ የምትመራው ሃገራችን በዘርና በቋንቋ ልዩነት ተብትበዋት እንደፈለጉ እያጨመላለቋት ይገኛሉ፡፡ በጣም የሚገርመው ደግሞ **426, 371 59 /** ያላት ሃገራችን 80 ሚሊዩን ህዝብ ለመመገብ ራሷን መቻል አቅቷት 4,5 ሚሊዩን ህዝብ ተራብ እጃችሁን ዘርጉልን ብሎ መጠየቅ እጅግ የሚያሳፍር ነው፡፡ የኔ ምኞት ሀገራችን የሰው ልጅ እንደፈለገ ተናግሮ ችግር ሳይኖር በሰላም ወጥቶ የሚገባበት ጊዜ እንዲመጣ ነው፡፡

# ጊዜው አሁን ነው

**Meron Berhane /ZEIL**

የወያኔ መንግስት የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ አሻንጉሊት ሲያጉሳቅል እነሆ ሁለት አሰርት ዓመታት ሆኖታል። ከምርጫ 1997 በኋላ መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ እየተበቀለ ይገኛል፡፡

ይባስ ብሎ አሁን ሕዝባችን በረሃብ እየረገፈ እንዲሁም በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ ይገኛል ባለንበት ጊዜ መሬታችን ለቻይና ለህንድ ለሳውዲ ኢንቨስተር ተሸጧል ገበሬው በነበረው መሬት /ቦታ/ ተፈንቅሎ በገዛ ሃገሩ /መሬቱ/ ላይ ለማኝ ሆኗል፡፡

ህዝባችን ከድህነት ከበሽታ ሊላቀቅ አልቻለም ይኸ ደግሞ የወያኔ/ ኢሕአዴግ/ መንግስት አገሪቱን ወደ ከፋ ደረጃ እያደረሳት ይገኛል፡፡

ስለዚህ እኛ በውጪ የምንኖር ኢትዮጵያኖች በአንድነት በመቆም ህዝባችንን ነጻ የምናወጣበት ጊዜ አሁን ነው፡፡እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ!

# የተዘባረቀ ህልም

**Tamerate Mulgeta/ Heppenheim**

እንደ ጠላቶቻችን ፍላጎት እና ምኞት ቢሆን ነጻነታችን ተገፎ በሌላ የውጭ ወራሪዎች እጅ በወደቅን ነበር፡፡

ነገር ግን የሃገሬ ህዝብ ከውጭ የሚሰነዘርበትን ማንኛውም ትንኮሳ ሳያስበረግገው በተረጋጋ መልክ በማሰብ አገር ውስጥ ያለውን ችግር ወይም ቅሬታ በመቻቻል ጎሳና ዘር ሳይለይ በህብረት በመነሳት በተለያየ ጊዜ ለነጻነቱ ሲያደርግ የቆየው ተጋድሎ ታሪክ ለዓለም ሲያወሳው የሚኖር ታላቅ እውነታ ነው፡፡

በአሁኑ ሰዓት ውድ ሃገራችን እጅግ አስጊና አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ነው የምትገኘው በወያኔ በአፈና ከንድ ታምቆ የተያዘውን የኢትዮጵያ ህዝብ ሁለንተናዊ ነጻነታችንን እውን ለማድረግ ከቦን ያለውን የድህነት እና የጭቆና ደመና ገፎ በሠላም በእኩልነትና በነጻነት እንድንኖር ብርቱ ትግል በማድረግ መስዋእትነትን መከፈሉ የሁሉም ዜጋ ድርሻ መሆን ይኖርበታል፡፡

በአንባገነኖች የሚጨፈለቀው የነጻነትና የመብት ጥያቄ የኢትዮጵያን ህዝብ በዘር በጾታ በሃይማኖት ሳይለያየው የበለጠ ህዝቡን አቆራኝቶታል፡፡

ስለዚህ ይህ ፈታኝ ግዜ ነው፡፡ የሀገሬ ህዝብ ሆይ በዚህ ፈታኝ ግዜ በአገራችን ላይ የሰላምና የዲሞክራሲ መሠረት እንዲጣል ቀጣዩን የትግል ግዜ እጅና ጓንት ሆነን መታገል ያስፈልገናል፡፡

# “በዲሞክራሲ ከለላ“

**Robel Beyene/Heppenheim**

የኢሕአዴግ መሪዎች በአፈሙዝ ስልጣን ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ በከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ የሃገራችንን መልክአ ምድርና ህዝብ በዘርና በጎሳ ሸንሽነዋል፡፡ የሃገሪቱን ህልውና ሊወስኑ የሚችሉ ብሄራዊ ጉዳዩች ሃላፊነት በጎደለው መንገድ በራሳቸው ጠባብ አላማና ለበላይ ገዢዎቻቸው

ሊጠቅም በሚችል ብቻ ከህዝብ እምነትና ፍላጐት ውጭ ሥራ ላይ እንዲውል አድርገዋል፡፡

ጉጠኝነትን የርእዩታቸው መሠረት ያደረጉት የወያኔ መሪዎች ይህንኑ በመንግስት ፖሊስነት በመቅረጽና ሥራ ላይ በማዋል ህዝባችንን በመከፋፈል ውድ ሃገራችንን ለውድቀት እያደረጓት ነው፡፡ እንደሚታወቀው ዘረኞች ከፋፋይ ሀይሎችና ጠባቂዎቻቸው ለሃገራዊ ስሜት ደንታ የላቸውም፡፡

ኢሕአፓ ግንባሩን ሳያጥፍ በተለያዩ አለም አቀፍ መድረኮች ላይ በመገኘት ዛሬ በኢትዮጵያችን የዘረኛው የወያኔ መንግስት ከህዝብ እምነትና ፍላጐት ውጭ ሃገርን የመበታተን ህዝብን እምነትና ፍላጐት ውጭ ሃገርን የመበታተን ህዝብን የመከፋፈል ፖሊሲ ከዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጋር የማይዛመዱና በትውልድ የወደፊት የመኖር ህልውና ላይ የተጠመዱ የጊዜ ቦምቦች መሆናቸውን አስረድቷል በወደፊትም ጥረቱ ይቀጥላል፡፡

# ወያኔ እጅህን ከሃይማኖቶች ላይ አንሳ!

Meseret Kebede/Hanna Nigusse-Arnsberg

አምባገነኑ የወያኔ ኢህአዴግ መንግስት በአገራችን ላይ ሲያደርስ የቆየው የተለያየ ግፍ ሳይበቃ አሁን ደግሞ በሃይማኖቶች ላይ እጁን መስደድ ጀምሯል።ብሎ ብሎ በቅርቡ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ቅዱሳን ገዳማት ላይ ታሪክ የማይሽረው ጠባሳ የጣለ ተግባር በማከናወን ላይ ነው።ስርዓቱ እጁን ያልሰደደበት ቦታ በኢትዮጵያ አይገኝም።

ቀጥሎም በእስልምና ሃይማኖት መጅሊስ ሹም ሽር ላይ እንዲሁም በስርዓታቸው ውስጥ በመግባት የሃይማኖት ተቋማትን የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ማስፋፊያው አድርጎ እየተጠቀመባቸው ነው።ይሄ ደግሞ የስርዓቱን አስከፊ ደረጃ ላይ መድረስ የሚያረጋግጥ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ በዚህ ስርዓት እየደረሰበት ካለው ግፍና መከራ በተጨማሪ ካድሬ አብያተ ክርስቲያናትና መስጊዶችን ማርከስ የለበትም።ኢትዮጵያዊ ደግሞ በአገሩና በሃይማኖቱ ከመጡበት ዝም ብሎ የሚያይ ባለመሆኑ በተለይ በውጭና በአገር ውስጥ የምንገኝ ሴቶች በስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ማሰማት ይጠበቅብናል።ምን እስከሚሆን ነው የምንጠብቀው?በዘር በሃይማኖት ተከፋፍለን ስንናቆር ያሳለፍነውን ጊዜ በማሰብ ኢትዮጵያውያን በፍቅር በአንድነት በመተሳሰብ በጋራ ልንታገል ይገባል።

ስለሆነም መላው ህዝብ በአምባገነኑ የወያኔ ስርዓት ላይ የተቃውሞ በትሩን ሊያነሳ ከአንድነት ሃይሎች ጋር በጋራ ሊታገል ይገባዋል።ኢትዮጵያን መድሃኒያለም ይባርካት!

# ሴቶችን ያላማከለው የወያኔ ፖሊሲ

**Semira Nigus/ HOF**

ላለፉት 21 የወያኔ አገዛዝ ዘመናት በሴቶች ላይ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር እየደረሰ ያለው ስቃይ እየተባባሰ ይገኛል።ለምሳሌ በአገር ውስጥ የሚከተሉት ወንጀሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፉ የመጡ ናቸው። 1- ያለእቻ ጋብቻ እና ተያይዞ የሚመጣው የፌስቱላ በሽታ 2- ጠለፋ 3- ተገዶ መደፈር 4- የተለያዩ አካላዊ ጥቃቶች እንዲሁም በአሲድ የሴት እህቶቻችንን ፊት ማበላሸት(Disfigurment)

ይህም የሚያሳየው የወያኔ ፖሊሲ ሴቶችን በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስኮች ላይ የሚኖራቸውን ሚና ግምት ውስጥ ያላስገባ ከመሆኑም ባሻገር በኣመት ባማካኝ 45 ሺ የሚሆኑ ሴቶች ሀገራቸውን ለቀው ወደ መካከለኛው ምስራቅ በቤት ሰራተኝነት ለማገልገል እንዲሰደዱ ምክንያት ሆኗል።

በስደት በሄዱበት አገርም በአሰሪዎቻቸው ለሚደርስባቸው ግፍና ስቃይ የወያኔ መንግስት ኤምባሲዎች በግዴለሽነት ስለሚያልፉት በእህቶቻችን ላይ የሚደርሰው ግፍ በሃገር ውስጥ ከሚደርሰው ስቃይ ጋር የማይተናነስ ሆኗል።ለምሳሌ በቤይሩት በኢትዮጵያ ቆንስላ ፅህፈት ቤት ፊት ለፊት በአሰሪዎቿ በግፍ ስትደበደብ የነበረችውና በማግስቱም ለህልፈት የተዳረገችው ኢትዮጵያዊቷ አለም ደቻሳ በቂ ማሳያ ናት።

ስለሆነም የሴቶች መብት የሚከበርባት የሴቶች ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ የሚረጋገጥባት ሃገር እንድትኖረን በጋራ ይህን አስከፊ የወያኔ መንግስት ልንታገለው ይገባል።

# ዴሞክራሲ የተፈጥሮ ፀጋ እንጂ የአምባገነኖች ችሮታ አይደለም!!

**Sara Mustefa Nuru/Germany**

በዴሞክራሲ ስም በስልጣን ላይ ያለው የኢህአዴግ መንግስት የዛሬ 21 ዓመት አንግቦት የነበረውን የዴሞክራሲ መፈክር በማየት ዴሞክራሲ የጠማው የኢትዮጵያ ህዝብ በእልልታ ነበር የተቀበለው።ነገር ግን ድብቅ ዓላማው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን መበታተን ነበር።

ይህ አምባገነን መንግስት ግን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የአገሪቱንና የህዝቡን ሃብት ለግል ጥቅሙ በማዋል ላይ ይገኛል።

በተለይም በህዝቡ ስም የሚገኘው የውጭ አገር ብድርና እርዳታ የስርዓቱ ባለስልጣናት በስማቸው በውጭ አገር ባንኮች እያከማቹ ህዝቡን ለከፋ ችግር እየዳረጉት ነው።ህዝቡ ግን በኑሮ ውድነት ምክንያት ምግብና የመኖሪያ ቤት በማጣት እየተሰቃየ ነው።

በዚህና በመሳሰሉት ችግሮች

ምክንያት ህዝቡ ተቃውሞውን ሲያሰማ ያለምንም ፍርድ ለእስርና ለእንግልት ይዳረጋል።የአምባገነኑ የወያኔ ድርጅት አባል ያልሆነ ሰው ምንም ቢማር ስራ የማግኘት ዕድሉ ፍፁም የሚታሰብ አይሆንም።ስለዚህ ህዝቡ በአገሩ ሰርቶ መኖር አልቻለም።በአጠቃላይ የዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቱ ስላልተከበረለት ይህንን ስርኣት ለማስወገድ እልህ አስጨራሽ ትግል ማድረግ ይጠበቅበታል።

# በታሪክ አሻራዎቻችን ላይ የሚደረገው ዘመቻ ይቁም!

**Tariku Abate/ HOF**

አምባገነኑ የወያኔ መንግስት በህገ መንግስቱ ላይ የሃይማኖት ነፃነትን ያወጀ ቢሆንም በተግባር ግን ከዚህ የተለየ ሆኗል።ለምሳሌ በክርስትና እምነት ተከታዮች ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውን የዋልድባ ገዳም ይዞታ የሆነና የቤተክርስቲያኒቱ ንብረት የሆነን ሰፊ መሬት በሃይል በመንጠቅ ለስኳር ልማት አውለዋለሁ በማለት በታሪካችንና ትውፊቶቻችን ላይ ሰፊ ዘመቻ ከፍቷል።

በተጨማሪም በምስራቁ የአገራችን ክፍል በሚገኘው አሰቦት ገዳም ለተነሳው የእሳት ቃጠሎ የመንግስት የእሳት አደጋ መስሪያ ቤት ዘገምተኛ ምላሽ እንዲሰጥ ከመደረጉም በላይ በፈቃዳቸው እሳቱን ለማጥፋት የተንቀሳቀሱትን ዜጎች አስሯል።

ስለሆነም ይህ ቅጥረኛ መንግስት የሀገራችንን የታሪክ አሻራ ከማጥፋቱ ቀድመን ልናስወግደው ይገባል።

# የፖለቲካዊ ስርዓት ተስፋ አስቆራጭነት

**Yonas Kibreab/München**

የኢትዮጵያ ሃገራችን የፖለቲካ ስርዓት ተስፋ አስቆራጭ እየሆነ መምጣቱን በግልፅ የሚያመለክቱ ድርጊቶች በመሃል አዲስ አበባ እየተፈፀመ አምባገነናዊዉ ስርዓት ምንም ጆሮ ሊሰጠዉ አልቻለም፤ ግድም የሚሰጠዉ አይመስልም። በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት የተረጋገጡ መሰረታዊ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሊከበሩ የሚችሉት ሃገሪቱ ዜጋ በመሆን ሳይሆን የአምባገነናዊ ስርዓቱ ገዢ ፓርቲ አባል በመሆን ብቻ ነዉ። የዜጎች የእለት ጉርስ፡ መጠለያ፤ እና አልባሳት በሙሉ በገዢዉ ፓርቲ እጅ ስለሆኑ ዜጎች ሳይወዱ ተገደዉ የአምባገነናዊ ስርዓቱ አባል ለመሆን ይገደዳሉ። ከጅምሩ ሳያምኑበት ተገደዉ የተቀላቀሉትን ስርዓት ዉስጡም ሆነዉ ሰላም ሊሰጥ ስለማይችል ክህሊና ጋር በሚደረግ ትግል አንዳንዶች ባለዉ ነገር ሁሉ ተስፋ ቆርጠዉ ራሳቸዉን በእሳት በማቃጠል ተቃዎሞአቸዉን በመግለፅ ላይ ቢገኙም ለሰብአዊ ክብር ቦታ የሌለዉ አምባገነናዊዉ ስርዓት እነዚህን ድርጊቶች ሁሉ እየተመለከተ እንኳ ለዜጎች እድል ለመስጠት፡ ሃሳብን በነፃነት ማራመድን ለመፍቀድ፡ የሰብአዊ መብቶችና ዴሞክራሲያዊ ስርኣት ተዋናዮችን በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ ለመፍቀድ፡ ፍፁም ዝግጁ አይደለም።

በዚህም የተነሳ ብዙ ተስፋ የቆረጡ ወጣቶች ራሳቸዉን በአደባባይ በእሳት እያቃጠሉ ሲሆን ለአብነት ማንሳት የምንችለዉ በቅርቡ ሚያዝያ 16/2004 ፒያሳ መሃል ራሱ ላይ ነዳጅ አርከፍክፎ ራሱን ያቃጠለዉ ዳዊት የተባለዉ ወጣት ይገኝበታል። በእዉነት አንድ ሰዉ ምን ተስፋ ቢቆርጥ ነዉ መሰል ድርጊት የሚፈፅመዉ? ድርጊቱን እጅግ አሳዛኝ የሚያደርገዉ የ30 ዓመቱ ወጣት ከዚህ በፊት በፖሊስነት ያገለግል የነበረና ለመንግስታዊ ስርዓቱ ምቹ ሆኖ ባለመገኘቱ የተባረረ እና የዛችን ሃገር የፍትህ ጉድለት በአይኑ እያየ ዉስጡ ሲደማ የኖረ መሆኖ ነዉ።

በአጠቃላይ ፖለቲካዊ ስርዓቱ እጅግ ተስፋ አስቆራጭ በመሆኑ ብዙ ዜጎች ሃገራቸዉን ለቀዉ ለመሰደድ ሌላዉ ደግሞ ከላይ እንደተመለከትነዉ ክቡር የሆነዉን ተፈጥሮአዊ ስብዕናዉን ነቆ ራሱን በአደባባይ ሲያቃጥል እንመለከታለን። በኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ዉስጥ ሰብአዊ መብቶችን ማክበርም ሆነ ማስከበር አንድም ከራሱ ከመንግስታዊ ስርዓቱ/ አብዮታዊ ዴመክራሲ/ አንድም ደግሞ ስርዓቱን ከሚመሩት አምባገነን ግለሰቦች ስግብግብ ፍላጎት አንፃር ሊሆን የማይችል ህልም ነዉ። አገዛዙ በአንድ ግለሰብ ፍላጎት ላይ የተንተራሰና ለየስሙላ በተደራጁ የፓርላማ፤ እና ፍርድ ቤቶች የታጀበ በመሆኑ ዴሞክራሲ ፅንሰ ሃሳብ ጠብታዉ እንካን ሊታይ አይችልም። ስለዚህ የወጣቱ ትዉልድ ያለዉ ብቸኛ ተስፋ ቢኖር የዚህን አምባገነናዊ ስርዓት እንደከዚህ በፊቶቹ ኢትዮጵያ አምባገነኖች ማስወገድና የህግ የበላይነትየሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መፍጥር አማራጭ የሌለዉ አማራጭ ነዉ እላለሁ።

# አምባገነኑ የወያኔ መንግስት እስከመቼ?

**Meriam Kuraw/WindsBach**

ለረጅም ኣመታት ህዝቡን በአሰቃቂና በግፍ በአፈና ረግጦ እየገዛ ሚገኘው የወያኔ መንግስት እስከመቼ ካሁን በሁዋላ ቤተሰብን እየበተነና በድብቅ እየገደለ በካድሬዎቹም ንፁሃን ምንም የማያውቁ እህቶቻችንን እየገረፈና እየቀጠቀጠ በመድፈር በዚህ አሰቃቂና ዘፀያፊ ተግባሩ እየገዛ እስከመቼ ይቀጥላል? አምባገነኑ የወያኔ መንግስት የህዝቡን ሰብዓዊ መብት በመንፈግ የዘር ማጥፋት ተግባሩን ተያይዞ በመቀጠል ላይ ይገኛል።ስለዚህ ይህን አሰቃቂ ጭፍጨፋ ማንኛውም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በሙሉ ይህን ጉዳይ ተመልክቶ በፍጥነት አንድ ውሳኔ ሊወስን ይገባል።

በቁጥር ይህ ነው የማይባል የንፁሃን ወገኖቻችን ደም በየስርቻው በከንቱ እንደቀላል እየፈሰሰ ይገኛል።በተለይም ህፃናት እህቶቻችን ሳይቀሩ በስርዓቱ ወታደሮች ተደፍረው ለስነ ልቦና ችግር ተዳርገው መኖራቸው የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ስለዚህ ይህን ጨካኝ የወያኔ መንግስት ለማስወገድ በጋራ ልንተባበር ይገባል!

# የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ውጤት በኢትዮጵያ

**Semira Mohammed/HOF**

ወያኔ እንደ ድርጅት ሲቋቋም የትናውን የፖለቲካ ፍልስፍና እንደሚከተል በተሳከረ ሃሳብ የነበረ ቢሆንም በመጨረሻ የአልባኒያን ኮሚኒዝም በመኮረጅ የድርጅት መርሁ አድርጎ ከመቀበሉም ባሻገር በአመራር ደረጃ ባሉ አባላቱ ሳይቀር ግልፅ ያልሆነ ማርክሲስት ሌሊኒስት ሊግ ትግራይ የሚል ቡድን በማቋቋም ይንቀሳቀስ ነበር። ነገር ግን በ1983 ወደ ስልጣን ሲመጣ ኮሚኒዝም በመላው ዓለም የወደቀበት ወቅት በመሆኑ ሌላ የፖለቲካ ፍልስፍና መከተል ነበረበት።በመሆኑም በመለስ ዜናዊ የተዘጋጀና የኮሚኒዝም አስተሳሰብ ቅጥያ የሆነ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የተባለ ፍልስፍና በሃይል በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ተጫነ።ይህንንም ለማስፈፀም የመከላከያ ሃይሉና የደህንነት መስሪያ ቤት ስርአቱን ብቻ እንዲያገለግሉ ተደርገዋል።

በመሰረታዊ አስተሳሰቡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከግለሰብ መብት ይልቅ በቡድን መብት ላይ የሚያተኩር በመሆኑ የግለሰቦችን ነፃነት የሚጋፋ ነው።ከዚህም በተጨማሪ የአንድ ፓርቲን ለረጅም ጊዜ በስልያን ኮርቻው ላይ መቆየት የሚደግፍና ለዚሁ የሚሰራ በመሆኑ የህዝብን የስልጣን ባለቤትነት የኒያሳጣ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ስርአት ነው።

በመሆኑም የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ማዳከም ምርጫ ማጭበርበር ሚዲያን በሞኖፖል መያዝና ሳንሱር ማድረግ ሌላው የስርአቱ መገለጫ ነው።

ስለሆነም የመለስ ዜናዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሃገራችንን ለአምባገነናዊ ስርዓት ድህነትና ለመበታተን አደጋ አጋልጧታል።

# በህዝብህ ላይ ጭካኔ

**Roza Agonafir Habte/ Germany**

የኢሕአዴግ መንግስት በኢትዮጵያ ስልጣን ከያዘ ግዜ ጀምሮ እያደረገ ያለው ተጽእኖና ኢ-ሰብአዊ ድርጊት በጣም የሚዘገንን እና ሃገሪቷን በዲሞክራሲና በልማት እንዳትገሰግስ እያደረገ ነው:: ለምሳሌ በእርሱ ሃሳብ አንድ የመንግስት ሰራተኛ በተቀጠረው የስራ ሞያ ሳይሆን የሚያገለግለው ለገዢው መንግስት ደጋፊና የገዢው መንግስት አላማ ብቻ የሚያራምድ መሆን አለበት። አለበለዚያ የሕብረተሰቡን ችግር የሚገልጽ ወይም ለህዝቡ የቆመ ከሆነ ግን ይህን ሰራተኛ ማግኘት የሚገባውን እንደ እድገት ስልጠና እንዳይሰለጥን ማስፈራራት ማሰር እንዲሁም ከስራ እስከ መባረር ይደርስበታል፡፡ ገዢው መንግስት እንደሚታወቀው በደሃው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ከተለያዩ የውጭ እርዳታ ድርጅቶች እርዳታ እየተቀበለ ለራሱ ጥቅም አገልግሎት ያውለዋል፡፡

ይሕን ዘዴ በመጠቀም ለደሃ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን በፕሮፓጋንዳ እየደለለ በቀን ሶስት ግዜ ትበላለህ ይሕን ይህን ይደረግልሃል በማለት ለህዝቡ አጉል ተስፋ በመስጠትና በማጭበርበር ስልጣኑን ያራዝማል ምስኪኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እንኳንም በቀን ሶስት ግዜ መብላት ቀርቶ አንዴም በጣም ከባድ ፈተና ሆኖበታል፡፡

በበሽታና በረሃብ እየተቀሰፈ እያየ አልደረሰለትም ስለዚህ ይህ አረመኔ እና ጨካኝ መንግስት እስከመቼ እንታገሰው?

# ዲሞክራሲ በጭልፋ

**Yergalem Heshe Abadde/ Germany**

ዲሞክራሲ ማለት እንደጽንስ ሃሳቡ ከሆነ Government of the people by the people to the people ነው::

ሕዝብ ያለምንም ተጽእኖ በነጻነት መብቱ ተጠቅሞ እራሱ በራሱ ሲተዳደርና የሚመስለውን ያለምንም ተጽእኖ በመብቱ ሲጠቀም ነው። ይህ ብቻ አይደለም የሰው ልጅ የመናገርና ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ ሕገመግስታዊ መብቱ ብቻ ሳይሆን ተፈጥሯዊ መብቱም ጭምር ነው:: ስለዚህ ሕዝቡ በአጠቃላይ የስልጣንና የልማት ባለቤትነት አለው ማለት ነው:: የኢሕአዴግ አንባገነናዊ መንግስት ግን ለስልጣን እድሜ ማራዘሚያና ለአላማው ስኬት ሃይል በመጠቀም ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ይጥሳል፡፡

የኢሕአዴግ መንግስት ሲፈልግ ስልጣን መብት ሊሰጥ ሳይፈልግ ደግሞ ሊከለክልህ በስመ ዲሞክራሲ እየነገደ የሚኖር መንግስት ነው:: ስለሃገርህ ጉዳይ የመናገርና የመጽሃፍ መብትህ ታፍኖ ያገባሃል አያገባህም ውጣ አትውጣ እያለ ምንም እንቅስቃሴ እንዳታደርግ አፍኖ የጋዜጦችና የመጽሄት ነጻ እድል በእጁ ይዞ ምን ላይ ነው ዲሞክራሲ፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት እራሱ ሕግ አውጥቶ ራሱ ያፈርሰዋል። በትክክል እንደ ሕገመንግስቱ ቢሆን ኖሮ ሕገ መንግስት የሕጐች ሁሉ የበላይ ሕግ ነው የኢሕአዴግ መንግስት ግን እንዳሻው ነው የሚያደርገው፡፡ በሃይል አማራጩ እየተጠቀመ በእስርና በዱላ መግዛት ነው የሱ አላማው። ስለዚህ እንዲህ አይነቱ የዲሞክራሲ ንግድ ለኢትዮጵያዊያን አያስፈልግም፡፡

# የዋጋ ንረት በኢትዮጵያ

**Addisalem Tegne Abera/ Kronach**

በአሁኑ ወቅት በሃገራችን እጅግ የሆነ የዋጋ ጭማሪ በእቃዎች ላይ ይታያል። ይህ የሆነበት ምክንያት ምን እንደሆነ አይታወቅም ለምን ቢባል ገዢው መንግስት አገሪቱን በዋጋ ማረጋጋት አልቻለም እጅግ የሆነ የዋጋ ጭማሪ ይታያል። ነጋዴው ለህብረተሰቡ የሚያቀርባቸው እቃዎች በአይነትም በመጠንም አንድ ሆኖ ዋጋው ግን በየወሩ ቢያንስ የ5 ብር ጭማሪ ይታያል ለምን ቢባል መልሱ መብቴ ነው ይልሃል አልያም እኔም የገዛሁት ውድ ነው አያዋጣኝም እቃ ጨምሯል ሌላም ሌላም ምክንያት በመደርደር ሕብረተሰቡ እየተመዘበረ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት በሃገራችን ኢትዮጵያ አንድ የመንግስት ሰራተኛ አራት ልጅ ካለው ቤተሰቡን ማስተዳደር አይችልም። ኑሮ ከብዶታል ጠቅላላ ለኑሮ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች በሙሉ

ከሕብረተሰቡ አቅም በላይ ሆኗል፡፡ ከብዙ በጥቂቱ ለኑሮ አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ዘይት እንውሰድ አንድ ሊትር ዘይት በኢትዮጵያ የሚሸጠው 50 ብር ነው፡፡ ታዲያ በዚሕ አይነት ሕብረተሰቡ ኑሮውን እንዴት አድርጐ መምራት ይችላል፡፡ ገዢው ወያኔ መንግስት ግን የሃገሪቱ ሕብረተሰብ በዚህ አይነት የኑሮ አረንቋ ውስጥ እየተሰቃየ በየአመቱ ሃገር አድጓል በማለት ለዜና ማሰራጫ ያስነግራል አገር ይደግ አገር ይልማ ነገር ግን አገርን የሚያለማ አገርን የሚያሳድግ ነዋሪው ሕብረተሰብ ነው፡፡ ታዲያ ይህ ህብረተሰብ ምን በድሎ ኑሮውን ያጨልምበታል፡፡

በኢትዮጵያ ሀገራችን ዛሬ ገበያውን እየተቆጣጠሩ ያሉት እጅግ በጣት የሚቆጠሩ የወያኔ ነጋዴዎች ናቸው፡፡ ታዲያ ሰማንያ ሚሊዩን ሕዝብ ይበልጣል በጣት የሚቆጠሩ የወያኔ መንግስት ነጋዴዎች ፍርዱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትቼዋለሁ፡፡

# የሴቶች መብት በኢትዮጵያ

**Almaz sebhat lema /Kronach**

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሃገራችን እየተፈጸመ ያለው የሴት ልጅ በደል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው ያለው ገዢው የወያኔ መንግስት የሴቶች መብት አስከብሪያለሁ በማለት የሃሰት ፕሮፓጋንዳውን በማወጅ ላይ ይገኛል፡፡ ነገር ግን አሁን እየተፈጸመ ያለው በደል እና ግፍ ብንመለከት እጅግ የሚዘገንን ነው ገና ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ሕጻናት የ6 እና የ7 ወር ሕጻናት ተደፍረው እየተገደሉ የውሃ መውረጃ ቱቦ ውስጥ እየተገኙ ነው። ይህ የሚያመለክተው በሃገሪቱ ምን ያህል ወንጀል እየተፈጸመባት መሆኑን የሚያስረዳ ነው። የወያኔ መንግስት ግን የሴት ልጅ መብት ተከብሯል ከማለት ውጭ ወንጀለኞችን አድኖ ለፍርድ እንኳን አላቀረበም። ሴት ልጅ በአግባቡ ትምህርቷን እንኳን ለመከታተል የማትችልበት ደረጃ ላይ ነው ያለችው፡፡ ከፍላጐቷ ውጭ በስለትና በገልሻለሁ ማስፈራራት ትምሕርታቸውን ለመማር ስለማይችሉ ለማቋረጥ ይገደዳሉ ከዛም የመጨረሻ እድላቸው ወደ አረብ ሃገር መሰደድ ይሆናል፡፡

የአረብ ሃገር ስደት እጣው ሁሉም የሚያውቀው ነው እንግልትና መደፈር መታሰር የፈላ ውሃ በላያቸው ላይ መደፋት ነው፡፡ እና ይህንን ያየና የሰማ የወያኔ መንግስት መልሱ በዝምታ ማለፍ ነው፡፡ ፍርዱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አበቃሁ

# የወያኔን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት እቅድ እንቋቋም!

**Yonas Addisu /Coburg**

ጥቂት የሚባሉት የአሁኖቹ የህወሃት አመራር አባላት እና ሌሎች ለእውነተኛ ነጻነት ሕይወታቸውን የሰጡ የሕወሃት አባላት ነጻነትን ተጠምተውና በወቅቱ ይዘውት የነበረውን ጭቆና ለማስወገድ የትጥቅ ትግል ከአርባ አመታት በፊት ከጅምሩም ከእውነተኞቹ ታጋዩችና ከነጻነት ታጋዩች እጅ ያመለጠው ትግል ዛሬ የውስጥ ጥላቻና ዘረኝነት በተጠናወታቸው ጥቂቶች እጅ ወድቋል። እነዚህ ጥቂቶች ይዘውት የተነሱትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በኢትጵያዊና በኢትዮጵያዊነት ላይ ያነጣጠረ መጠነ ሰፊ ሴራ የፈፀሙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ለእውነተኛ ትግልና አላማ የተነቃነቁትን በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በመግደል በማሠርና ከአገር እንዲሰደዱ በማድረግ የኢትዮጵያውያን ሃብትና ንብረት በቀጥታና በተዘዋዋሪ በመዝረፍ በመበዝበዝና በመቆጣጠር ኢትዮጵያውያን ያለውዴታቸው በግዴታ የንብረታቸው ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ተደርገዋል።

አገሪቷ ለብዙ ዓመታት ተከብራ የኖረችበትን አንድነት ለማፈራረስ የጐሳና የሃይማኖት ግጭትን በመቀስቀስ ቀጣይ የከፋፍለህ ግዛ ሴራቸውን ለማጠናከር ሲሉ አገሪቷን ከመቼውም ግዜ በላይ ለትልቅ አደጋ አጋልጠዋታል። በተለይም በአሁኑ ሰአት የኢትዩጵያ ህዝብ ከየትኛውም የዓለም አገሮች የማይወዳደር ጭቆና ስደት ድህነት ግድያ እስራትና ነጻነት ማጣትና ሙስና የተስፋፋበት አገር ለመሆን በቅታለች። በየትኛውም መለኪያ እነዚህ በህዝብ በአገርና በህገመንግስት ጠባቂነት ስም በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ትልቅ አደጋ ለመጣል እየተንቀሳቀሱ ያሉት ጥቂት የህወሃት አባላት አገሪቷን የማይወክሉ ለ40 ዓመታት ይዘውት የተነሱትን አገርንና ህዝብን የመበታተን ሴራ ከግብ ለማድረስ የሚንቀሳቀሱ ስግብግቦች ሲሆኑ የነዚህን ዘረኞች ግብ ለማክሸፍ ግዜው አሁን ሲሆን ማንኛውም ጉዳዩ የሚያሳስባቸው ዜጐችና ለኢትዮጵያ መኖር የምንመኝ ሁሉ በአንድነት እነዚህን ጥቂት ዘረኞች ለመቋቋም በጋራ መነሳት ይኖርብናል፡፡

# እውነት የምንሰማው መቼ ነው

**Metasebia Kiflu / Kronach**

አምባገነኑ የወያኔ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ የሕዝቡ እውነተኛ መረጃ የማግኘት መብት ተገፏል፡፡ በተጨማሪም ወያኔ እሱ ከሚፈልገው መንገድ ውጪ ምንም አይነት መረጃ ወደ ሕዝብ የሚያደርስ የፕሬስ ድርጅትን እንደ ጠላት መፈረጁን ተያይዞታል፡፡ በተለይም ከምርጫ 97 በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ የግል ፕሬስ ነጻነት ሙሉ በሙሉ ተዘግቷል፡፡ ይባስ ብሎ ህዝብ እውነተኛ መረጃ የሚያገኝበትን የቮይስ ኦፍ አሜሪካን እና የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥንን /ኢሣት/ ጃም ማድረጉ ግልጽ ነው፡፡ በአንጻሩ ግን ህዝብ የሚፈልገውን መረጃ የማግኘት ሙሉ መብት እንዳለው እራሱ ወያኔ ለይስሙላ በጻፈው ህገ መንግስት ላይ ቢኖርም ዛሬ ዛሬ አለም አቀፍ ሚዲያዎችን ማዳመጥ እንደ ወንጀለኛ የሚቆጠርበት ጊዜ ስለሆነም በአሁኑ ወቅት የመገናኛ ብዙሃን ነገር ሙሉ በሙሉ በመንግስት እጅ ሆኗል፡፡ ለህዝቡ እውነታውን ይዘግቡ የነበሩ የግል ጋዜጦችን ለምን እውነታውን ለህዝብ አሳወቃችሁ በሚል ጋዜጠኞችን አስሯል ከእስር የተረፉትም ለሕይወታቸው አስጊ በመሆኑ የሚወዱትን ሃገርና ህዝብ

ጥለው እንዲሰደዱ አድርጓል፡፡ ሃገሪቷ ላይ ያለው ህዝብ እውነት መስማትን እየናፈቀ ኑሮውን ይገፋል፡፡

# ወያኔና የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መሪ እጅና ጓንት መሆናቸውን ያውቃሉ?

**Surafel Tekleab Fentawn / Tirschenreuth**

ጤና ይስጥልኝ ለጥላ መጽሄት አዘጋጆች በቅድሚያ እንኳን ለጌታችን ለመድሃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የትንሳኤ በአል በሰላም አደረሳችሁ እያልኩ ሃሳቤን እንደሚከተለው እገልጻለው፡፡

እነሆ ቅድስት አገራችን ኢትዮጵያ ለብዙ ዘመናት በስልጣን ላይ ያሳለፈቻቸው መንግስትም ሆኑ የሃይማኖት መሪዎች ለሀገራቸውም ሆነ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን የነበራቸው የሃገርና የእምነት ፍቅር የጐላ ነበር፡፡

በአሁኑ ዘመን ግን ይባስ ብሎ የወያኔ መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ በመግባት በደርግ መንግስት ጊዜ የነበሩትን የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መሪ ያለምንም ጥፋት የእኔ ጐሳና ዘር አይደሉም ፖለቲካዬን ያበላሹብኛል በማለት ፓትርያርኩን ከመንበራቸው በማውረድ ሃገር ለቀው እንዲወጡ ካደረገ በኋላ የራሱ ተከታይ የሆኑትን ሰው ያለምንም የሕዝብ ምርጫ ለራሱ ለፖለቲካውና የሃገሪቱን ቅርስ ለመዝረፍ እንዲመቸው ማን አለብኝ በማለት አምጥቶ አዲስ ፓትርያርክ መሾሙ ይሕ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የታወቀና አወዛጋቢ ጉዳይ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

በእኒህ ፓትርያርክ መሾም በጐሣ ልዩነት የተነሣ ብዙ ሊቃውንቶች ስቃይና መከራ ችግር እየደረሠባቸው ይገኛሉ፡፡

የሃይማኖት መሪውም የወያኔ መንግስትን መከታ በማድረግ በእየቤቱ ክርስቲያኑ የራሳቸውን ጐሣና ዘር እንዲሁም ቲፎዞዎችን ስልጣን በእየቦታው በመስጠት የቤተክርስቲያኗን ሃብትና ንብረት በመዝረፍ ለራሳቸው ጥቅም ላይ በማዋላቸው ብዙ ካህናቶችንና ሕብረተሰቡን በሙሉ እያወዛገበ ይገኛል፡፡

የቤተክርስቲያኗ የቀኖና ህግ አንድ ፓትሪያርክ በህይወት እያለ እሱን አስወግዶ በላዩ ላይ ሌላ ፓትርያርክ መሾም አይፈቅድም የወያኔ መንግስት ግን ይህን ሕግ እያወቀ ህጉን በመጣስ በራሱ በመተማመን የራሱን ደጋፊ ሾመ።

ለአቡነ መርቆሪዎስም መባረር ምስክርነት በወቅቱ የነበሩት የሃገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ታምራት ላይኔ በጃንዋሪ ወር 2009 ዓ,ም ለአሜሪካው አምባሳደር በሰጡት ዝርዝር መግለጫ ላይ ኦርጂናሉ ፓርትያርክ እንዲባረር ሰነድ ላይ መፈረማቸውን መስከረዋል፡፡

በተጨማሪም የአቡነ መርቆሪዎስ መወገድም ሆነ የአቡነጳውሎስ መሾም የፖለቲከኞች ውሣኔ መሆኑ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ አቡነ ጳውሎስ ካለው መንግስት ጋር እጅና ጓንት ሆነው የሚሰሩ ሲሆን በሕዝቡም ዘንድ በፖለቲካ አቋማቸው ምክንያት ጥላቻ ያተረፉ ስለመሆናቸውም ጨምረው ተናግረዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ የወያኔ መንግስት ከዚህም አልፎ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የረሃብ እና የስራ አጥ ቁጥር እለት ተእለት እየጨመረ ሲሄድ ምንም አይነት መፍትሄ መስጠት እንዳልቻለና ሕዝቡም ራሱ ያለበትን የፖለቲካ ችግር በሚዲያ መግለጽ እንዳይል ነጻነቱን ተነፍጐና ተከልክሎ ይገኛል በመሆኑም ኢትዮጵያ ውስጥ ምንም አይነት ዲሞክራሲም ሆነ መፍትሄ ፍትህ የለም፡፡

አንድ ሰው የመንግስት ተቃውሞ እንቅስቃሴ ሲያደርግ ከተገኘ በማሰር በመደብደብ ከዛም አልፎ የሞት ፍርድ በመፍረድ ብዙ ስቃይና መከራ በሕዝቡ ዘንድ እየደረሰ ይገኛል፡፡

እንዲሁም የመንግስት ሠራተኛው ነጋዴው አርሶአደሩ ሁሉም ሕብረተሰብ በስራ ድርሻው የወያኔ አባል ካልሆናችሁ ከስራ ትባረራላችሁ ግብር ያለ አግባብ ይጨመርባችኋል መሬት አታገኙም የያዛችሁትንም መሬት ትቀማላችሁ በማለት በአፈ ሙዝ በማስፈራራት በውዴታ ግዴታ ህገ መንግስቱን ትደግፋላችሁ በማለት ሕዝቡም ለመኖር ሲል እየተገደደ ሳይፈልግ በግድ አባል የሚሆንበት ደረጃ ላይ ነው ያለው።

እነሆ የኢትዮጵያ ሕዝብ መከራና ስቃይ ጭቆና እና በደል እንግዲህ ይብቃ በማለት "ሳንፈልጋቸው ሃያ ዓመታቸው እንደጋዳፊ ላይ ቀርላቸው" የሚለውን መፈክር በማንገብ ትግላችን ግብ እንዲመታ እግዚአብሄርን በመለመን ዘርና ጐሳ ሃይማኖትና ቀለም የማይለያይ መንግስት እንዲሠጠን በጸሎት በመማጸን እንጠይቅ በማለት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሪዬን አስተላለፋለሁ፡፡እግዜአብሄር አምላክ ኢትዮጵያን ለዘላለም ይጠብቅልን!

# የመኖሪያ ቤት መስሪያ መሬት ምሪት በኢትዮጵያ

**Fisshatsion Hailegeberile /Kronach**

በአሁኑ ወቅት በሃገራችን ሀብታምም ሆነ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘው ህብረተሰብ መሬት አግኝቶ የመኖሪያ ቤት ለመስራት እጅግ ከፍተኛ ውጣ ውረድ እንዳለበት ይታወቃል፡፡ ለምን ቢባል ጠቅላላ የመሬት መብት ያለው በክልል ባለስልጣናት እጅ ነው፡፡ የወያኔ መንግስት ይህን ያደረገው ባለስልጣናቱን እና ተከታዮችን ታማኝ እንዲሆኑት በጥቅማጥቅም የተያዘ ስለሆነ የመሬት ምሪትን በተመለከተ ግልጽ የሆነ ተጠያቂነት ያለበት አሠራር የለም፡፡ ለመጥቀስም ያህል በአንድ ክ/ከተማ የመሬት ጉዳይ በተመለከተ ሥራውን እንዲሠሩ የሚደረጉት ለአስተዳደሩ እና ለባለስልጣናት ቅርብ የሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም የክፍለ ከተማው አስተዳደር ለሙስና ያመቸው ዘንድ የመሬት ምሪት እና መሃንዲሱን ለእርሱ ቅርብ የሆኑ ሰዎችን ካደረገ በኋላ በከተማ ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች በማደን በተለያዩ ሰዎች ካርታ እና ፕላን እንዲዘጋጅ በማድረግ መሬቱ በከፍተኛ ብር ይሸጣል፡፡

ከዚህም ሽያጭ የተገኘው ብር ለባለስልጣናቱ በተዋረድ ይከፋፈላል፡፡ በዚህ ሁኔታ ከሚፈጸመው ሙስና ሃገሪቱ ምን ያህል ጥቅም እያጣች መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ከብዙ በጥቂቱ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ ውጪ በክልል እየተደረገ ያለውን ግፍ ቢቻል ያለመስማቱ ይመረጣል ለምን ቢባል ለብዙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን የራስ ህመም ሆኖባቸዋልና፡፡

እኛ ግን እንዲህ አይነቱን የሃገርን ንብረት መበዝበር ለአለም እናሣውቃለን። የክልል መሬቶች ጠቅላላ ተሸንሽነው በባለስልጣናት እጅ ስር ናቸው፡፡ የተሸጠው ተሸጧል የቀረው በዝቅተኛ ኑሮ ሚኖረው ህብረተሰብ የያዘው የይዞታ መሬት ብቻ ነው፡፡ መሬት የመሸጥ አባዜ የተጠናወታቸው የወያኔ መንግስት ባለስልጣናት የህብረተሰቡን ይዞታ የሆነን ንብረት የናንተ መሬት ለልማት ይፈለጋል በሚል ሰበብ ህብረተሰቡን ምንም አይነት ተለዋጭ መሬትም ሆነ ካሣ ሳይከፍል ከነባር ይዞታቸው በማፈናቀል ህብረተሰቡን ለሰቃይ እየዳረገው ይገኛል፡፡ ለልማት ይፈለጋል የተባለው መሬት ተሸጦ ለባለስልጣናቱ ይከፋፈላል፡፡ ከሁሉም በላይ ከመሬት ጋር በተያያዘ ጉዳይ የሃገሪቱ እድገት የኋልዩሽ ሆኗል፡፡

በአንጻሩ ግን የወያኔ ባለስልጣናት እና ተከታዩቻቸው የገቢ ምንጫቸው ጨምሯል፡፡ ከዚህም በተረፈ የሚበቃቸውን ያህል ለልጅ ልጆች የሚሆን ጥሪት አከማችተዋል፡፡ የሚያሳዝነው ግን የወያኔ መንግስት ይሕ ሁሉ አልበቃ ብሎት ጠቅላላ በሃገሪቱ ውስጥ ያለውን መሬት በሊዝ ይሁን ብሎ አዋጅ አውጥቶአል፡፡ በአዋጁ ደግሞ በዝቅተኛ ደረጃ የሚኖረው ህብረተሰብ መተዳደር አይችልም ኑሮውም ከብዶታልና እናም ገዥው የወያኔ መንግስት እና ተከታዮቹ እኛ ከኖርን ማንም መኖር አይችልም እያለ ይገኛል፡፡ ስለዚህ ፍርዱን ለእግዚአብሄር እና ለአለም ሕዝብ ትተነዋል፡፡

# ነጻነት ወይስ ባርነት

Dawit Tesfaye /Hadamar

ከ1983 ዓ,ም ጀምሮ ለነጻነታችሁ ታገልኩላችሁ በማለት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚቀልደው የወያኔ ድብቅ ሴራ ተደብቆ የማይቀር ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ከሶስት ሺህ ዓመት በላይ በዘር በሃይማኖት በጐሣ ሳይከፋፈል አንድነቱን ጠብቆ መቆየቱ ለማንም የኢትዮጵያ ህዝብ የተደበቀ ታሪክ አለመሆኑ ታሪክ ይዘክራል፡፡ ነገር ግን የወያኔ መንግስት የኢትዮጵያ ታሪክ ወደ ጐን በመተው የራሱን የስልጣን ጊዜ የማራዘም ከምርጫ 97 ዓ,ም ጀምሮ ጥንት አባቶቻችን ለትውልድ ጥለውት ያለፉትን ታሪክ ወደ ጐን በመጣል በዘር በሃይማኖትና በጐሳ በመከፋፈል የራሱን አንባገነንነትና ዘረኛነቱን በገሃድ አውጥቶታል፡፡ ይህውም የራሱን ስልጣን ለማቆየት ከዘጠኝ አመት ህጻን ልጅ እስከ አረጋውያን ድረስ በራሱ ታማኝ ወታደሮች ተገድለዋል፡፡ የንጹሃን የኢትዮጵያ ልጆች ደም አፍስሷል፡፡ ይህ ደግሞ ዘመን የፈጠረበት ሳይሆን ወያኔ የራሰን አንባገነንነት ያንፀባረቀበትና የስልጣን ጊዜውን ማራዘሚያ ያደረገበት የታሪክ ጠባሳ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለማንም ለምንም ኢትዮያዊ ከህሊናው የማይጠፋ ቁስል ብቻ ሳይሆን መርዝያ ጭስ መሆኑ ህሊና ያለው ልብ- ልብ ይላል፡፡

ዛሬ ለኢትዮጵያ ህዝብ ነጻነት እኩልነት የሃይማኖት የጐሳ ልነዩት ሳይኖር ተቻችሎ በመኖር በዲሞክራሲ መንገድ ለሃገር ክብር ሲባልና የህዝባችንን መብት ለማስከበር ከደም መስዋትነት እስከ ህልፈተ ሕይወት መስዋትነት በመክፈል የዜግነት ግዴታቸውን በመወጣት ግንባር ቀደም ሆነው የወያኒ የታሪክ አዳፋ ለማጽዳት ደፋ ቀና በማለት ቁርጠኝነታቸውን እያሳዩ ይገኛሉ፡፡ ለአብነት ያህልም ወያኔ ስልጣኑን በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንደ ማይለቅ የተገነዘቡ የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር በሰሜን ጐንደር በወልቃይት በጠገዴ በአርማጨ በሁመራ እንዲሁም በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች በሽምቅ በመግባት የወያኔን ውድቀት ለማጣደፍ በሰፊው ዘመቻ ተያይዞ ይገኛል፡፡

የታሪክ አተላ የሆነው የወያኔ መንግስት ለመጣል ምንም አማራጭ የሌለው የትጥቅ ትግል መሆኑን የተገነዘቡ ንጹህ የኢትዮጵያ ልጆች የዜግነት ግዴታቸውን እየወጡ መሆኑን በቁርጠኝነነት ሲያሳዩን እኛም ከጐያቸው በመቆም ዘረኛውን ወያኔ ከጭንቅላታችን አውርደን በመጣል የዜግነት ግዴታችንን በመግለጽ ከጐናቸው ልንቆምላቸው ይገባል፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብን በሃይማኖት በጐሣ በዘር መከፋፈሉ ብቻ ሳይሆን የብቀላ መረቡን በሰፊው በመዘርጋት በኢኮኖሚ በማህበራዊ ህይወት በመከፋፈል የራሱን የአገዛዝ ጊዜ ከግብረአበሮቹ ጋር በመሆን ለማራዘም እሰራ ይገኛል።

